# የቃል ግጥሞች ማኅበራዊ ፋይዳ - በደቡብ ወሎ ቦረና ወረዳ አርሶ አደሮች ማንጸሪያነት

# The Social Benefits of Oral Poetry: Reflections of Farmers' Life in South Wollo, Borena District

**ሰይድ ይማም[1]፣ ዘሪሁን አስፋው[2] እና ሙሐመድ አሊ[3]**

**Seid yimam, Zerihun Asfaw, and Mohammed Ali**

**አጠቃሎ**

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደቡብ ወሎ ቦረና ወረዳ በሚገኘው አርሶ አደር ማኅበረሰብ ከሚከወኑት ቃል ግጥሞች ማኅበራዊ ፋይዳ ባላቸው ላይ የይዘት ትንተና ማካኼድ ነው፡፡ ጥናቱ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲኾን፣ ቃል ግጥሞችን ከመስክ ለመሰብሰብ ተግባር ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ደግሞ ቃለ መጠይቆችና ሰነዶች ናቸው፡፡ በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች በገላጭ የምርምር ዓይነት ይዘታቸው ተተንትኗል፡፡ በትንተናው ወቅት ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ (Functional Theory) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ከይዘት ትንተናውም ቃል ግጥሞቹ የማኅበረሰቡን መልካም ዕሴቶች የማስተማር ፋይዳ ያላቸው መኾኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በዚህም ግብረ ገብነትን በሚያንጸባርቁ ቃል ግጥሞች አማካይነት ልጆችን እና ወጣቶችን በማስተማር ገና ከለጋነታቸው ጊዜ ጀምሮ ባሕርያቸውን መቅረጽ እንደሚገባ መረዳት ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቃል ግጥሞቹ በሥራ የመትጋትን ጥቅም ለማኅበረሰቡ የማሳወቅ ፋይዳ እንዳላቸው ተስተውሏል፡፡ ይህ ዓይነቱ ፋይዳ በኅብረተሰቡ ዘንድ የሥራ ፍቅር እንዲኖር ስለሚያደርግ ለኢኮኖሚውና ለማኅበራዊው ልማት የሚያበረክተው አስተዋፅኦ እጅግ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ቃል ግጥሞቹ መጥፎ ባሕርያትን የመግታት ፋይዳ እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህ መሠረት በስንፍና፣ በዳተኝነት፣ በሐሜት፣ በክሕደት፣ በአመንዝራነት፣ ጠንቋይን በማመን፣ በመታበይ (በመኩራት)፣ በሙስና፣ በመሳሰሉት መጥፎ ተግባራት ላይ የተዘፈቁ ሰዎች አድራጎታቸውን ለመቆጣጠርና ለመግታት ሲባል በቃል ግጥሞች አማካይነት በማኅበረሰቡ ሲወገዙ ተስተውሏል፡፡ በመጨረሻም የሥነ ማኅበረሰብ፣ የሥነ ሰብና የታሪክ ምሁራን ማኅበራዊ ፋይዳን በተመለከተ የተነገሩ ሌሎች ቃል ግጥሞችን ከመስክ ሰብስበው ጥናት ቢያደርጉ የወረዳውን ማኅበረሰብ ታሪክ፣ ማኅበራዊ ሕይወት፣ ባህልና ሥነ ልቡና፣ ወዘተ. የበለጠ ለመገንዘብ ያስችላል የሚል ይሁንታ በአጥኚው ቀርቧል፡፡

**ቁልፍ ቃላት፡- ቃላዊ ግጥም፣ ማኅበራዊ ፋይዳ፣ መልካም ዕሴቶች፣ መጥፎ ባሕርያት**

[1] በአዲስ አበባ ዩነቨርሲቲ በፎክሎር የዶክትሬት ዲግሪ ተማሪ: yimamseid59@gmail.com

[2] በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሰብዓዊነት፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጋዛጠኝነትና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ መምህር የነበሩ፡፡

[3] አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሰብዓዊነት፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጋዛጠኝነትና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ:- mohanebat@yahoo.com

**Abstract**

The primary objective of this study is to conduct a content analysis of the social benefits of oral poems performed within the farming community of the Borena District in South Wollo. The study employed a qualitative research methodology, utilizing interviews and document analysis as data collection methods to gather oral poems from the field. The collected poems were subsequently analyzed using descriptive research, guided by functional theory. The content analysis revealed that oral poems serve several key social functions. Primarily, they are instrumental in teaching and reinforcing the community's positive values. The findings suggest that by transmitting moral lessons to children and youth, oral poems play a crucial role in shaping character from an early age. Furthermore, the analysis indicates that oral poems promote a strong work ethic by informing the community of the importance of hard work. This benefit fosters a collective appreciation for labor, which is highly valued for its contribution to both economic and social development. Conversely, it was found that oral poems also function to curb negative social behaviors. The study observed that individuals engaged in detrimental acts—such as laziness, dishonesty, gossip, betrayal, adultery, belief in witchcraft, arrogance, and corruption—are often subject to social condemnation through these poems, which serve to control and restrain such conduct. Finally, the researcher suggests that further collection and study of oral poems concerning social benefits by sociologists, anthropologists, and historians would provide deeper insights into the history, social life, culture, and mentality of the district's community.

**Keywords:** oral poetry, social benefit, good values, bad character

## 1. መግቢያ

ቃል ግጥም በቃል ተደርሶ በቃል የሚከወን እና በቃል የሚተላለፍ ነው እየተባለ ቢነገርም በተጻፉ ሥራዎችም ውስጥ ሊገኝ እንደሚችልና ዐብሮ እንደሚኖርም Finnegan (1974:58) ገልጸዋል፡፡ ብዙውን ጊዜ ቃል ግጥም ህልውናው ከዘፈን፣ ከሙሾ፣ ከእንጉርጉሮና ከዜማ ጋር መኾኑ የሚታወቅ ነው፡፡ በዓለም ላይ

በተለያዩ ከዋኞች የሚቀርቡት ቃል ግጥሞች ልዩ ልዩ ፋይዳዎች አሏቸው፡፡ ከእነዚህ መካከል ለፈጣሪ ምስጋናን ለማቅረብ፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ ከሚታዩት ፍርሃቶች፣ ከግጭቶች፣ ወዘተ. ራስን ለመጠበቅ ያገለግላሉ (Alembi, 2002:49)፡፡ ታሪክን ለመመዝገብ ወይም ሰንዶ ለማስቀመጥና ፖለቲካዊ ሚናን ለመጫወትም ይውላሉ (Finnegan, 1970:83)፡፡ Kabira እና Mutahi (1988:50) በበኩላቸው ቃል ግጥሞች ተማሪዎችን የማስተማር፣ ማኅበረሰብን የማስጠንቀቅ፣

መረጃዎችን የማቀበል፣ የማዝናናት፣ ባህልን የማሳደግና ለሚቀጥለው ትውልድ የማስተላለፍ፣ የመምከርና የማሰልጠን ፋይዳ እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡
ከላይ እንደተገለጸው ልዩ ልዩ ፋይዳዎች ያሉት ቃል ግጥምም ኾነ አጠቃላይ የሥነ ቃል ጥናት በምሥራቅ አፍሪካ የተጀመረው በ0ሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ አካባቢ ነው (Peek እና Yankah,2004:209)፣ (ፈቃደ፣1991፡43) እና (Finnegan, 2012:30)፡፡ በዚህ ወቅት የአውሮፓውያን ተጓዦች፣ የወንጌል ሰባኪዎች፣ የቋንቋና የሥነ ሰብ ምሁራን ትረካዎችን፣ ዘፈኖችን፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን እና ሌሎች ዘውጎችን ሰብስበዋል (Finnegan,1974፡53)፡፡ እነዚህ የሥነ ቃል ሰብሳቢዎች የየራሳቸው የኾኑ ዓላማዎች ነበሯቸው፡፡ ከእነዚህ መካከል ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋትና የቅኝ ግዛት ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ ባላቸው ፍላጎት እንደኾነ ይታወቃል፡፡ በተለይ የምሥራቅ አፍሪካን ቋንቋዎችን እና ባህሎችን ለመረዳት ሲሉ ንጽጽራዊ ጥናት ለማካኼድም ችለዋል (Peek እና Yankah, 2004: 209)፡፡

በኢትዮጵያም እስከ 1950 እና ከዚያ ወዲህም ቢኾን በራሳቸው ፍላጎት ተነሣሥተው የሀገራቸውን የቋንቋና የባህል ቅርስ ለወጣቱ ትውልድ የማስተላለፍ ዓላማን በተግባር ለመተርጎም የሥነ ቃል ዘርፎችን ሰብስበው ያሳተሙ ሰዎች እንዳሉ ፈቃደ (1991፡43) ገልጸዋል፡፡ ይህ ተግባር አሁንም ድረስ ቢኾን በከፍተኛ ኹኔታ ሊጨምር እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ እስከ 1990ዎቹ መጨረሻ ድረስም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ከ137 በላይ በቃል ግጥሞች ላይ ብቻ ጥናቶች እንደተሠሩ ተረጋግጧል (ፈቃደ ፣1991፡ 45)፡፡ ጥናቱ ትኩረት ባደረገበት በወሎ ቦረና ወረዳ ግን በየትኛውም የትምህርት ደረጃ በአርሶ አደሩ ማኅበረሰብ የተገጠሙ ቃል ግጥሞች ተሰብስበው ማኅበራዊ ፋይዳቸው አለመጠናቱን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ጥናት ተቋም ሥር ባለው ቤተ መጻሕፍት፣ በዞኑና በወረዳው የባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤቶች ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ በዚህ መሠረት ጥናቱ ባካለለው ወረዳ በማስተርስና በዶክትሬት ዲግሪ ባሉ የትምህርት ደረጃዎች በማኅበረሰቡ አንደበት እየተነገሩ ያሉ ቃል ግጥሞች ከመስክ ተሰብስበውና በዘውግ ተከፋፍለው ማኅበራዊ ፋይዳቸው የተተነተነበት ምርምር አለመካሄዱ ይህን ጥናት ለመሥራት አነሣሽ ምክንያት ሆኖኛል፡፡

እዚህ ላይ ማስገንዘብ የምፈልገው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥር የሚገኘው ማኅበረሰብ ተመሳሳይ የሆነ የህይወት ልምድ ያለው በመሆኑ ቃል ግጥሞቹ የተሰበሰቡበት ወረዳ ሐብት ብቻ ነው ማለት ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም ኅብረተሰቡ የጠበቀ ባህላዊ፣ መልክዓ ምድራዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ግንኙነት ስላለው ቃል ግጥሞችም ከቦታ ቦታ፣ እንደዚሁም ከገጠር ወደከተማ ተስተላልፎ ሊኖራቸው እንደሚችል መገንዘብ ይገባል፡፡ የጥናቱ ዓላማም በወሎ ቦረና ወረዳ አርሶ አደሮች የተገጠሙ ቃል ግጥሞችን በቃለ መጠይቅና በሰነድ ሰብስቦ በፈርጅ በፈርጅ በመመደብ በማኅበራዊ ፋይዳዎቻቸው ላይ የይዘት ትንተና ማካኼድ ነው፡፡

## 2. የጽንሰ ሐሳብ ቅኝት

በዚህ ርእስ ጉዳይ ሥር ስለቃል ግጥም ምንነት፣ ቃል ግጥምን ለመበየን መሠረታዊ ስለሆኑ ነገሮችና ስለቃል ግጥም ማቅረቢያ ስልቶች አጫጭር ማብራሪያዎች የቀረቡ ስለኾነ ቀጥሎ እንመልከት፡፡

### 2.1. ቃል ግጥም

ቃል ግጥም ሙዚቃዊነት በሚሰማባቸው በዘፈን፣ በቀረርቶ፣ በእንጉርጉሮ፣... የሚከወኑ ጥበቦችን የሚጠቀልል ዕሳቤ ነው (Berhanu,1998፣31) :: ጥበቡ በቃል ተደርሶ ሊቀናበርና ሊተላለፍ የሚችለውም ያለ ምንም የጽሕፈት አገልግሎት ነው እየተባለ ሲገለጽ ቢቆይም ዘርፉን ሙሉ በሙሉ ሊበይን አይችልም፡፡ ምክንያቱም በአሁኑ ወቅት የተለያዩ የቃል ግጥም ዘርፎች ከጽሕፈት ጋር እየተቀናበሩ በመቅረብ ላይ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል፡፡ የቃል ግጥም አደራረሱም ኾነ ክዋኔው በማንኛውም ቡድን ወይም ኹነት የተገደበ አይደለም (Peek and Yankah,2004:991)፡፡

ቃል ግጥም በርካታ ፋይዳዎች ያሉት መኾኑን Bascom (1954፡343-349)፣ Bauman (1971፡38—39)፣ Douglas (2000፡84) እና Dundes (2007:56) ገልጸዋል፡፡ ይህ ጥናት በተካኼደበት ወረዳ በሚገኙ አርሶ አደሮች አንደበት የተቀነቀኑት የቃል ግጥሞችም የማኅበራዊ መልካም ዕሴቶችን የማስተማር፣ በሥራ የመትጋትን ጥቅም የማሳወቅና እኩይ የኾኑ ባሕርያትን የመግታት ፋይዳዎች ያሏቸው መኾኑን ለመመርመር ተችሏል፡፡

#### 2.1. 1. ቃል ግጥምን ለመመደብ መሠረታዊ የሆኑ መስፈርቶች

ቃል ግጥምን ለመመደብ ድረሳ፣ ተስተላልፎና ክዋኔ መሠረታዊ መስፈርቶች መኾናቸውን Morris and Jean “Binta” Breeze (2004) እና Finnegan (1970፡17-20) ገልጸዋል፡፡ በተለይ Finnegan ለእነዚህ ሦስት መሠረታዊ መስፈርቶች የሰጧቸውን ማብራሪያዎች በሚከተለው መልኩ ጨምቆ ለማቅረብ ጥረት ተደርጓል፡፡

1. ድረሳ፡- በቃል ብቻ የተቀነባበረውን የድረሳ ዓይነት የሚመለከት ነው፡፡ የድረሳው ኺደት ከክዋኔው ድርጊት ቀዳሚና በስፋት የተለየ ሊኾን ይችላል፡፡ ስለዚህ ቃላዊ ድረሳ ከክዋኔ በፊትና በክዋኔ ወቅት ያለውንም ኺደት ያካትታል (Finnegan, 1970፡18)፡፡ እዚህ ላይ እንዴት ነው ቃል ግጥም የሚደረሰው? የሚለው ጥያቄ ሊነሣ ይችላል፡፡ በዚህ መነሻነት ከዋኙ የተሰጠውን አሐድ በቃሉ አጥንቶ በማስታወስ ነው? ወይስ ኹኔታው በተሟሟቀበት ጊዜ ወዲያውኑ አዘጋጅቶ ነው የሚያቀርበው? ወይም አንድ ወጥ የኾነ የድረሳ ስልት አለ ወይ? የሚሉ ጥያቄዎች በተደጋጋሚ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ሰዎች የተለያዩ ተግባራትን እያከናወኑ፣ እየጠጡ፣ የሞተን ሰው እየቀበሩ፣ እየጸለዩና የንጉሣዊ ቤተሰብ አባላት እየተዝናኑ ባሉበት ወቅት የደረሷቸውን ቃል ግጥሞች ሌላው ሰው የቅርብ ተሳታፊ ኾኖ

ሊያዳምጣቸው ይችላል፡፡ በእነዚህ አጋጣሚዎች የሚቀርቡ ዘፈኖች፣ ዜማዎች፣ ዝማሬዎች፣ የጋለ ስሜት ንግግሮች፣ ወዘተ. ኢ-መደበኛ ለኾነው ስልጠና ምቹ ኹኔታን ስለሚፈጥሩ ለክወና ብቁ የኾነ ሰው በቃሉ አጥንቶ በማስታወስ ሌላ ጊዜ ሊከውናቸው ይችላል ማለት ነው (Alembi, 2002፡37)፡፡

2. **ተስተላልፎ፡-** ቃል ግጥም አፋዊ በኾነ መንገድ የመተላለፍ ባሕርይ እንደነበረው ለረጅም ዘመናት ሲገለጽ ቆይቷል፡፡ በቅርብ ወቅት ግን በአቀንቃኝ አማካይነት በቃል የተፈጠረው ቃል ግጥም ተስተላልፎው በታተሙ መጻሕፍት ወይም በዘመናዊ የትምህርት ማስተማሪያ መሣሪያዎች ሊኾን እንደሚችል Finnegan (1970፡19) ገልጸዋል፡፡ አሁን አሁን ላይ ደግሞ በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ዘዴዎች ሳይቀር የቃል ግጥም የሽግግር ተግባር በመከናወን ላይ መኾኑን የዚህ ጥናት አንባቢ የሚገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በሀገራችንም የጀግናን መንፈስ በሚጠሩ ጽሑፋዊ ግጥሞችና ባህላዊ ሙዚቃዎች ውስጥ ከትውልድ ወደትውልድ ሲተላለፉ የነበሩ የቃል ግጥሞችን በንባብ ኺደታችን ልናገኛቸው፣ በእዝነ ኅሊናችንም ልናዳምጣቸው እንችላለን፡፡ ገጣሚያኑ ይህንን የሚያደርጉት ለግጥሞቻቸው ማካኼጃ ብቻ ሳይኾን ለአንባቢ ሊነግሩት የፈለጉትን ጭብጥ ለማስረገጥ ሲሉ እንደኾነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

3. **ክዋኔ፡-** ቃል ግጥም ተከዋኝ ነው፡፡ አንድን አጋጣሚ ሰበብ በማድረግ ነው በአቀንቃኙ የሚከወነው፡፡ ይህ ማለት ያለ ምክንያት ስለማይከወን በዋናነት ምክንያትን ይፈልጋል ማለት ነው (Finnegan, 1970:21)፡፡ በክዋኔው ወቅት እንደ ቃል ግጥሙ ዓይነት ቃል አልባ የኾኑ አሐዶች በአጃቢነት ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ለአብነትም ዐውድን ጠብቀው በሚከናወኑ የእርሻ ተግባራት አገልግሎት የሚሰጡ የማምረቻ መሣሪያዎች፣ አልባሳት፣ ዱላ፣ ቃጭል፣ ታምቡር፣ ከበሮ፣ በገና፣ መለከት፣ ጥሩንባ፣ ክራር፣ ደወል፣ የእጅ ጭብጨባ፣ ወዘተ. ያሉት አጃቢ ኾነው ይቀርባሉ (Alembi, 2002, 35)፡፡ የክዋኔውና የአጃቢዎቹ መቀላቀል በአድማጩም ኾነ በከያኒው ላይ ከፍተኛ የኾነ ተጽዕኖ ያሳድራሉ (Olajubu, 1978:24-25), (Okpewho 1985:9) እና (Miruka. O, 1994:8)፡፡

### 2.1.2. የቃል ግጥም ማቅረቢያ ስልቶች

ቃላዊ ግጥሞችን ሳቢና ቀላል የሚያደርጉ ስልቶች እንዳሉ Finnegan (1970), Okpewho (1985 & 1992) ያስረዳሉ፡፡ እነዚህም ስልቶች ድግግሞሽ፣ ትይዩነት (parallelism)፣ የድምፅ ቃና፣ ዘይቤዎች፣ ሙዚቃዊ ምት (ዜማዊነት)፣ የድምፅ ቅንብር (alliteration) እና በጥንቃቄ የተመረጡ ቃላት ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት ትንተና ውስጥ ተግባር ላይ የዋሉት ድግግሞሽና ዘይቤዎች በመኾናቸው እነሱን በተመለከተ የቀረቡትን አጫጭር ማብራሪያዎች ቀጥሎ እንመልከት፡፡

***ድግግሞሹ-*** Finnegan (1970፡90) በአብዛኛው የቃል ግጥም ጉልህ ገጽታው ድግግሞሽ ነው ይላሉ፡፡ ምንም እንኳን ድግግሞሽ የሁሉም ግጥም አካል ቢኾንም የቃል ግጥሞች ድግግሞሾች ግን በሐረጋት፣ በስንኞች ወይም በአዝማቾች ላይ

የተመሠረቱ ናቸው፡፡ Miruka (1994:90) እና Okpewho (1985:9) እንደገለጹት ድግግሞሽ፦

- ክዋኔውን ለማስረዘም፣
- የግጥሙን ጉዳዮች ለማጠንከርና ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ትኩረት ለመስጠት፣
- ለክዋኔው የሙዚቃውን (የግጥሙን) ምት ለመጨመር፣
- ለግጥሙ መዋቅር አስተዋጽኦ ለማድረግ ያገለግላል፡፡

***ዘይቤ፦*** እንደ ጽሑፋዊ ግጥም ሁሉ ቃል ግጥምም ዘይቤን ማዕከል የሚያደርግ መኾኑ የታወቀ ነው፡፡ ምክንያቱም ቃል ግጥሙ አንድነቱን እንዲጠብቅ፣ ጥልቀት ያለው ትርጉም እንዲሰጥ ለማድረግና ውበትን የተላበሰ እንዲኾን ሲባል ነው (Finnegan, 1970:113)፡፡ ስለዚህ ተለዋጭ፣ ሰውኛ፣ አነጻጻሪና ግነት ዘይቤዎች በአብዛኛው በቃል ግጥም ውስጥ አገልግሎት ላይ ይውላሉ:: በአጭሩ ያለ ዘይቤያዊ ቋንቋና ገለጻ፣ ውበትና ማዝናናት የቃል ግጥሞች ውጤት አይኖራቸውም (Finnegan,1977:113-118)፡፡

## 3. የምርምሩ ንድፈ ሐሳብ

በዚህ ጥናት በቃለ መጠይቅና በሰነድ ፍተሻ የተሰበሰቡትን ጥሬ መረጃዎች በተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ (Functional Theory) በመተንተን ጥናቱ የመጨረሻው ውጤት ላይ እንዲደርስ ጥረት ተደርጓል፡፡ ንድፈ ሐሳቡ በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ የተጀመረና ማንኛውም የሥነ ቃል ዘርፍ ተግባር አለው በሚለው አስተሳሰብ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ይኼውም አንድ ተመራማሪ የሚሰበስበው ማንኛውም ቃል ግጥም፣ ምሳሌያዊ አነጋገር፣ ተረት፣ ሚት፣ ዘፈን፣ ወዘተ. ባህላዊ፣ ማኅበራዊና ሥነ ልቦናዊ ተግባር ያለው መሆኑን Green (1997:386) ገልጸዋል:: Bascom (1954:343-349) ደግሞ በማኅበረሰብ ውስጥ ቀጣይነት ያለውን የሥነ ቃል ኹኔታ ለመግለጽ የሚያገለግሉትን በርካታ ተግባራትን በዝርዝር አቅርበዋል፡፡ ኾኖም ይበልጥ ትኩረት የሰጡት ሥነ ቃል የማምለጥ፣ የአንድን ነገር ተገቢነት የማጽደቅ፣ የማስተማር፣ የመቆጣጠርና የመግታት ተግባራት ያሉት መኾኑ ላይ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ለዚህ ጥናት ለመረጃ መተንተኛነት ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ የተመረጠበት ዋናው ምክንያት በቦረና ወረዳ ከሚገኘው አርሶ አደር ማኅበረሰብ የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች ያላቸውን ይዘት መርምሮ ማኅበራዊ ፋይዳቸውን ለማወቅ ከፍተኛ የኾነ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

## *4. የጥናቱ ዘዴ*

ይህ ጥናት ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን ተከትሏል፡፡ በዚህ መሠረት ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎችም ኾኑ የትንተና ውጤቶቹ በቁጥር የሚገለጹ ወይም የሚወከሉ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም አጥኚው መረጃዎቹን ተንትኖ የጥናቱን ውጤት ላንባቢ የሚያቀርበው ትረካዊ ወይም ገለጻዊ መንገድን ተከትሎ በመኾኑ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ገላጭ የምርምር ዓይነት በተግባር ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ ይህ የኾነበት ምክንያት ከመስክ በቃለ መጠይቅና በሰነድ የተገኙትን መረጃዎች በትንተና እና በገለጻ ለማቅረብ ስለሚያስችል ነው፡፡ በቃለ መጠይቅ ቃል

ግጥሞችን ከመስክ ለመሰብሰብ በወረዳው ውስጥ ከሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል ዐሥራ አምስት ሰዎች በዓላማ ተኮርና በጥቆማ የናሙና ዘዴዎች ተመርጠው በመረጃ ሰጪነት እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ ጥናቱ ከተካኼደበት ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት በባህል ዕሴት ዘርፍ ሠራተኛ አማካይነት በተለያዩ አጋጣሚዎች የተሰበሰቡ የቃል ግጥሞችን በወረቀትና በ Soft copy[4] ለማግኘት ተችሏል፡፡

## 5. መረጃ ትንተና

እንደሌሎቹ የሥነ ቃል ዘርፎች ቃል ግጥምም በርካታ ፋይዳዎች ያሉት መኾኑን ቀደም ሲል ለመግለጽ ተችሏል፡፡ ይህ ጥናት በተካኼደበት ወረዳ በሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች አንደበት የተቀነቀኑት የቃል ግጥሞችም  የተለያዩ ፋይዳዎች ያሏቸው መኾኑን ለመመርመር ተችሏል፡፡ በዚህ መሠረት በቃል ግጥሞቹ አማካይነት የተገኙት ፋይዳዎች በሚከተለው ኹኔታ ቀርበዋል፡፡

### 5.1. ጀግንነትን ቀጣይ የማድረግ ፋይዳ

ቃል ግጥሞች ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው ፈጸሟቸው የሚባሉትን የጀግንነት ተግባራት ለተከታዩ ትውልድ በማስተላለፍ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ማድረግ ይችላሉ፡፡ በዚህ መሠረት በሀገራችን ጀግና የኾኑትን ሰዎች የቆራጥነት፣ የጽኑ እምነት፣ የታጋይነት፣ ወዘተ. ትእምርት (symbol) መኾናቸውን በማሳየት አርኣያነታቸውን ዘላለማዊ የማድረግ ኃይል አላቸው ማለት ይቻላል፡፡ ከእነዚህ ጀግኖች መካከልም ድምፃውያን ሕዝባዊ በኾኑ የቃል ግጥሞቻቸው አማካይነት ስሙን እያወደሱ፣ በሕይወት በኖረበት ወቅት የፈጸማቸውን ተግባራት እያወሡ ያዜሙለትን በላይ ዘለቀን እናገኛለን፡፡ በቦረና ወረዳ የሚኖሩ አርሶ አደሮችም ቢኾኑ ስለበላይ ዘለቀ የጀግንነት ተግባራት ያቀነቀኗቸውን ቃል ግጥሞች ቀጥለን እንመልከት፡፡

*ቃል ግጥም 1፡- የእነ በላይ እናት የመነመነችው*
*በርበሬዋን ወልዳ ባሊያንን ፈጀችው፡፡*
*(ቃለ መጠይቅ፣ ይመር አሰን፣ 20/05/2012)*

በቃል ግጥሙ ውስጥ "እናት" የሚለውን ቃል በመጀመሪያው ስንኝ ላይ እናገኛለን፡፡ ቃሉ ደግሞ ሦስት ነገሮችን ይጠቁመናል፡፡ አንደኛው አንዲት ሴት ከወለደችው ልጅ ጋር ባላት የተዛምዶ ግንኙነት የምትጠራበት መኾኑን ያመለክታል፡፡ ኹለተኛው ደግነትን፣ ሩኅሩኅነትን፣ ወዘተ. ያሳየናል፡፡ ሦስተኛው ደግሞ ሕዝቦች በውስጧ ለሚኖሩባት፣ የተወሰነ ጂኦግራፊያዊ ክልልና አንድ መንግሥታዊ አስተዳደር ላላት ሀገር በተምሳሌትነት ይቆማል፡፡ በመጀመሪያው ትርጉም መሠረት "የእነ በላይ እናት … ሲል የበላይ ዘለቀን እናት እመት ጣይቱ አሰኔን እንዲናስብ ያደርገናል፡፡ በመኾኑም ሴትዮዋ ትክለ ሰውነታቸው የከሳ፣ የቀጠነና የኮሰመነ ቢኾንም ከአብራካቸው የተወለዱት በላይ ዘለቀና እጅጉ ዘለቀ ግን በበርበሬ በመመሰል ባሕር

[4] Soft copy :- ዲጂታላዊ ቅጅ ፣ በኮምፒውተር ሊነበብ የሚችል ጽሑፍ የሚለውን ትርጉም ይረዷል፡፡

አቋርጦ የመጣውን የጣሊያንን ጦር በኃይል ወግተው መፍጀታቸውን ወይም መጨረሳቸውን ቃል ግጥሙ ያስገነዝበናል፡፡ በሦስተኛው ትርጎማ መሠረት እናት በሀገር ተምሳሌትነት ስትቆም ደግሞ ከበላይ ዘለቀ ጋር የጀግንነትን ባሕርይ ተላብሰው በአርበኝነት ዘመናቸው አኩሪ ታሪክ የሠሩት ጀግኖች ዛላው በድልህ፣ በአዋዜ ወይም በዱቄት መልክ ተዘጋጅቶ ሲበሉት በሚፋጅ ወይም በሚያቃጥል በርበሬ ተወክለው ጠላትን በመጨረስ ታላቅ ተጋድሎ መፈጸማቸውን እንገነዘባለን፡፡ በዚህ መሠረት ቃል ግጥሙ ጀግኖቹ እንዲዘከሩ፣ ተጋድሏቸውም ቢኾን ለቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፍና አርኣያነታቸውም ቀጣይነት እንዲኖረው አድርጓል ማለት ይቻላል፡፡

*ቃል ግጥም 2፡- ጥጡም ተወደደ ከበደ ሸሬታው*
*አንድ ሱሪ ነበር በላይ አስወደደው፡፡*
*(ከባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 22/05/2012)*

በቀድሞ ጊዜ የቤት እመቤቶች በቆላ አካባቢ የሚበቅለውን ጥጥ ጊዜ ፈጅተው በመዳመጥ፣ በማባዛት፣ በመፍተል፣ እንደዚሁም ድርና ማግ አድርገው በሸማኔ በማሠራት የራሳቸውንም ኾነ የቤተሰቦቻቸውን ዕርቃን ለመሸፈን፣ ኀፍረተ ሥጋቸውን ለመሰወር ይችሉ ነበር፡፡ በዚያን ወቅት ከላይ የተዘረዘሩትን ኺደቶች አልፎ ለቀሚስ፣ ለነጠላ፣ ለእጀ ጠባብ፣ ለሱሪ፣ ለጋቢ፣ ወዘተ. አገልግሎት ይውል የነበረው ጥጥ ዋጋው በመናሩ የተነሣ በገንዘብ አማካይነት ሸሬታ (ልውውጥ) ለማካኼድ እጅግ በጣም ማስቸገሩን ቃል ግጥሙ ያመላክታል፡፡ በዚህ ምክንያት የሚለበስ ልብስ መጥፋቱን፣ አንድ ሱሪ በገበያ ላይ ቢገኝ እንኳ በላይ ዘለቀ በውድ ገዝቶ መታጠቁን እማሬያዊ በኾነ ፍች እንገነዘባለን፡፡ ጥናቱ በተካኼደባቸው ወረዳዎችም ኾነ በሌላው የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ማኅበረሰብ ዘንድ ግን ሱሪን በጀግንነት ይፈክረዋል (ይተረጉመዋል ወይም ይፈታዋል)፡፡ ለአብነትም ”ሱሪ ታጠቀ“ ሲባል ወንድ ወጣው፣ የጀግንነት ሞያ ሠራ ማለት እንደኾነ መረዳት ይገባል፡፡ በዚህ መሠረት በላይ ዘለቀ የታጠቀው ሱሪ የጀግንነት ትእምርት መኾኑን ቃል ግጥሙ ማሳየት ችሏል፡፡

የቃል ግጥሞች በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ ገናን የጀግንነት ተግባራትን ቀጣይነት እንዲኖራቸው እንደሚያደርጉ ቀደም ሲል ተመልክተናል፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ በኅብረተሰቡ አንደበት የሚቀነቀኑት የቃል ግጥሞች በየዘመናቱ ገዥ የኾኑ መንግሥታት ”አልጋዬን ይነቀንቃል“ ብለው በጠረጠሩት ጀግና ላይ የሚወስዱትን ርምጃ ማንጸባረቃቸው አይቀሬ ነው፡፡ አቶ አሰን እንድሬ መስከረም 07/ 2013 ዓ.ም በነገሩኝ መሠረት በ1933 ዓ.ም የኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ከኢትዮጵያ ተጠራርጎ እንደወጣ ሌሎች ሹማምንት የተሻለ ሹመት ሲያገኙ በላይ ዘለቀ ግን ከዓመት በኋላ የቢቸና አውራጃ አስተዳዳሪ ኾኖ ተሾመ፡፡ ግለሰቡ ለሀገሩ ጽኑ እምነት የነበረው፣ ኃይለኛ፣ ጠላቱን በቆራጥነት የተዋጋ ቢኾንም፣ ይህ ዓይነቱ የጀግንነት ድርጊቱ ካልተዋጠላቸው ከዘመኑ ሹማምንት ጋር አለመግባባት ተፈጠረ፡፡ በኋላ ላይም በባንዳዎች አቀናባሪነት ንጉሠ ነገሥቱ ጦር አዘመቱበት፡፡ ከዚያም ሶማ በተባለው በረሓ አስከፊ የኾነ ውጊያ እየተደረገ ሳለ ለድርድር ከመንግሥት በተላኩ ካህናት አማካይነት አባ ኮስትር በላይ እጁን እንዲሰጥ ተደረገ፡፡ በመጨረሻም ሀገሪቷ

በነበራት ልዩ ፍርድ ቤት በስቅላት እንዲቀጣ ስለተወሰነበት ጥር 5 ቀን 1937 ዓ.ም ማተቡ ገመድ ኾኖ ስቅላቱ ተፈጸመበት በማለት አቶ አሰን እንድሬ በዝርዝር ገልጸዋል፡፡ ይህንኑ አሳፋሪ ድርጊት የሚያመለክቱትን የቃል ግጥሞች ቀጥለን እንመልከት፡፡

*ቃል ግጥም 3፡- ፈሪ ንጉሥ ፈርቶ ከባንዳዎች ጋራ*
*አርቀው ሰቀሉት እንዳይንጠራራ፡፡*
*(ከባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 22/05/2012)*

እንደ አሰን እንድሬ ገለጻ በላይ ዘለቀ "ንጉሡን ተቃውሞ በመሸፈት አልጋቸውን ሊነቀንቅ ነው" የሚለው የተሳሳተ መረጃ ለኢጣሊያ መንግሥት ዐድረው በነበሩት ባንዳዎች አማካይነት በዘውዳዊ አስተዳደር ዙፋን ላይ ተቀምጠው ለነበሩት ለዐፄ ኃይለ ሥላሴ ይነገራቸዋል፡፡ እሳቸውም የሀገሪቷ የሕዝብ እረኛ፣ አውራ፣ መሪና ዐሳዳሪ መኾናቸው የሚታወቅ ቢኾንም በባንዳዎቹ በተነገራቸው የተሳሳተ መረጃ የተነሣ በከፍተኛ ኹኔታ ፍርሃት እንዳደረባቸው ቃል ግጥሙ ያመለክታል፡፡ በዚህ ምክንያት ወዳጆቻቸው ለኾኑት ባንዳዎች ሹመትና ሽልማት ሲሰጡ ጠላቴ ነው ብለው የፈረጁትን በላይ ዘለቀን ግን በቀላሉ ከማይደረስበት ቦታ ላይ ተሰቅሎ እንዲገደል ማድረጋቸውን ታሪክ ነጋሪ ከኾነው ቃል ግጥም መገንዘብ እንችላለን፡፡

*ቃል ግጥም 4፡- አሳዘነኝ በሬው አሳዘነኝ ከሞቱ አሟሟቱ*
*አልቆረጥ አለ ገመዱ ካንገቱ፡፡*
*(ቃለ መጠይቅ፣ ሙሐመድ ይማም፣ 20/05/2012)*

በዚህ ቃል ግጥም የመጀመሪያው ስንኝ ላይ "በሬ" የሚለው አሐድ ተጠቅሷል፡፡ አሐዱን እማሬያዊ በኾነ መልኩ ስንመለከተው ከቀንድ ከብት ወገን የኾነ፣ ብዙውን ጊዜ ለእርሻ ሥራ የሚያገለግል የቤት እንስሳ መኾኑን እንረዳለን፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አሐዱን "ጀግና" በሚለው መፌከር እንችላለን፡፡ በዚህኛው ትርጓሜ ለሀገሩ፣ ለወገኑ መሥዋዕትነት ከፍሎ ጥሩ የጀግንነት ተግባር ላከናወነው በላይ ዘለቀ በውክልና ቆሟል፡፡ በመኾኑም ይህ ጀግና ከቃጫና ከሌሎች ነገሮች ተሸርቦ በተዘጋጀው ጠንካራ ገመድ ተሰቅሎ ነፍሱ ከሥጋው እንዲትለይ ወይም ሕይወቱ ፍጻሜዋን እንዲታገኝ ለማድረግ ሲባል ክፉ ነገር መሠራቱ አስተከዘኝ፣ አስከፋኝ፣ አስቀየመኝ፣ ወዘተ. በማለት የቃል ግጥሙ ባለቤት አቀንቅኗል፡፡ እኛም በላይ ዘለቀ በዐንገቱ ገመድ ገብቶ ክፉ አሟሟት እንዲሞት መደረጉና አስከሬኑንም በስለት ቆርጦ ማላቀቅ አለመቻሉ ትልቅ ቅሌትና ውርደት መኾኑን እንገነዘባለን፡፡

## 5.2 መልካም ዕሴቶችን የማስተማር ፋይዳ

በወረዳው የሚኖረው አርሶ አደር ጠቀሜታ ያላቸው መልካም ዕሴቶች (ስጦታዎች) ያሉት መኾኑን በቃለ መጠይቅ ከተሳተፉት መረጃ ሰጪዎች የተገኘው ጭምቀ ሐሳብ ያስረዳል፡፡ እነዚህ መልካም ዕሴቶችም በቃል ግጥሞች ተንጸባርቀዋል፡፡ በዚህ መሠረት ሞራልን ወይም ግብረ ገብነትን፣ እንደዚሁም ጥሩ ወይም መልካም ሥራን የሚያንጸባርቁ ዕሴቶችን በቃል ግጥሞች አማካይነት ልጆችን እና ወጣቶችን በማስተማር ገና ከለጋነታቸው ጊዜ ጀምሮ ባሕርያቸውን መቅረጽ

ይቻላል፡፡ በዚህም ምግባረ መልካምና ትሑት ትውልድን ማፍራት ይቻላል፡፡ ስለዚህ ቃል ግጥሞቹ ማኅበረሰቡ የተስማማባቸውን መልካም ዕሴቶች ተከታዩ ትውልድም ተቀብሎ በተግባር ላይ እንዲያውላቸው ያደርጋሉ ማለት ነው፡፡ ከመስክ ከተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች መካከል የማኅበራዊ መልካም ዕሴቶችን የማስተማር ፋይዳ ካላቸው መካከል ጥቂቶቹን ቀጥለን እንመልከት፡፡

*ቃል ግጥም 5፦ አይሰርቅ አይቀማ እንደ ጎረምሳ*
*አባቱን በጅል የማያስነሣ፡፡*
*(ቃለ መጠይቅ፣ በለጠ አደላ፤ 22/05/2012)*

በጎ ምግባርን ለማስተማር በማኅበረሰቡ አንደበት የሚነገሩት ቃል ግጥሞች ልጆች ከለጋ ዕድሜያቸው ወቅት ጀምሮ የሰውን ንብረት በመዝረፍና በመቀማት በእኩይ ተግባር ላይ እንዳይሰማሩ ያስተምራሉ፡፡ የፉከራ ቃል ግጥሙን የነገረኝ ጎረምሳም ምግባሩ የቀና በመኾኑ እንደ ሌሎቹ ዕድሜ እኩዮቹ በመስረቅና በመቀማት ወላጆቹን በክፉ የማያስነሣ መኾኑን አመላክቷል፡፡ በዚህ የተነሣ በቃል ግጥሞች አማካይነት ልጆች ወላጆቻቸውን በመጥፎ እንዳያስጠሩና በክፉ ነገርም እንዳያሳሙ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ በዚህ ዓይነት ኹኔታ ያደጉ ልጆች በተራቸው ዐዋቂ ኾነው ወልደው ሲከብዱ በቃል ግጥሞች አማካይነት ልጆቻቸው ከንቱ የኾኑ ነገሮችን እንዳይከተሉ ይመክሯቸዋል፤ ያስተምሯቸዋልም፡፡ ይህ ዓይነቱ ማኅበራዊ መልካም ዕሴት እንዲህ እንዲህ እያለ ሲተላለፍ እውነተኛና ደግ የኾነ ትውልድን ማፍራት ይቻላል ማለት ነው፡፡

*ቃል ግጥም 6፦ ዱብ ዱብ እንደ ወጥ ሠሪ*
*ለባልንጀራው ቁም ነገር ሠሪ፡፡*
*(ቃለ መጠይቅ፣ ሰሚራ ጌቶ፣ 21/05/2012)*

በቃል ግጥሙ ውስጥ ያለው ገጸሰብ በፉከራ የዜማ ስልት ዱብ ዱብ ማለቱን ገልጿል፡፡ በዚህ አካላዊ እንቅስቃሴውም ከላይና ከታች ተፍ ተፍ በማለት ጣት የሚያስመጥጥ ወጥን ከሚያዘጋጅ ሰው ጋር በንጽጽር ቀርቧል፡፡ ዱብ ዱብ ማለቱ ደግሞ ለባልንጀራው ጠቃሚ የኾነ ነገር በሚሠራበት ወቅት መኾኑን መረዳት እንችላለን፡፡ ምክንያቱም ጥናቱ በተካኼደበት ወረዳ ያሉ የማኅበረሰብ አባላት በተለያዩ አጋጣሚዎች ለልጆቻቸው "በመከራና በጭንቅ ቀን ጥሎህ ከሚሸሽ ሰው ጋር ባልንጀራ አትኹን፤ እንደዚሁም በመከራና በጭንቅ ቀን ባልንጀራችሁን አትጣሉት፡፡ ባልንጀራችሁን በሙሉ ልባችሁ ከወደዳችሁት በመከራችሁ ቀን አይለያችሁም" በማለት ማኅበረሰቡ መልካም የኾኑ ማኅበራዊ ዕሴቶችን በማስተማር ላይ እንደሚገኙ በመስከረም 07/2013 ዓ.ም በተካኼደው ቃለ መጠይቅ ተሳታፊ የነበሩት አቶ አብዱ ሰይድና ሁሴን አደም ገልጸውልኛል፡፡ ከላይ ያለውን ቃል ግጥም የነገረኝ ግለሰብም የማኅበረሰቡ አባል እንደመኾኑ ማንኛውም ሰው ለጓደኛ ወይም ለባልንጀራ ጠቃሚ የኾነ ጉዳይ ወይም ቁም ነገር ማድረግ እንደሚገባ ሐሳቡን በማስተማሪያነት ማቅረቡን መገንዘብ እችላለን፡፡ ይህ ዓይነቱ ቃል ግጥም "ባልንጀራህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ" ከሚለው ከፈጣሪ ትእዛዝ ጋር በጣም ቁርኝት ያለው በመኾኑ ሰዎች በመተጋገዝ፣ በመረዳዳትና በመተሳሰብ እንዲኖሩ በማስተማር መልካም የኾነው የማኅበረሰብ ዕሴት ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ ይችላል፡፡

*ቃል ግጥም 7፦ ትከሻው ደማቅ እንደ ጨረቃ*
*የተናገረው አንዱ የሚበቃ፡፡*
*(ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 22/05/2012)*

ዘይቤዎች ለቃል ግጥሞች ርእሰ ጉዳይ ማንጸሪያ መኾናቸው የሚታወቅ ነው፡፡ ምክንያቱም ግጥሞቹ ጥልቀት ያላቸው ትርጉሞችን እንዲሰጡና ውበትን የተላበሱ እንዲኾኑ ለማድረግ ሲባል እንደኾነ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ በዚህ ግጥምም የሰው ትከሻና ጨረቃ በንጽጽር ቀርበዋል፡፡ እንደሚታወቀው በሌሊት ወቅት ሙሉ የኾነችው ጨረቃ ከፀሓይ የምታገኘውን ብርሃን ወደመሬት በምትፈነጥቅበት ወቅት በሰማይ ላይ ጎላ ብላና አምራ፣ ደምቃ የምትታይ አካል ናት፡፡ በንጽጽሩ መሠረት በቃል ግጥሙ የተሳለው ገጸሰብ ትከሻም የጎላ፣ ያማረ፣ እንደ ጨረቃ ብርሃን ደምቆ የሚታይ መኾኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ዓይነት ትክለ ሰውነት ያለው ሰው ሐሳቡን ለሌላው አካል በሚገልጽበት ወቅት በንግግሩ ወጥ የኾነ አቋም እንዳለው፣ የመጨረሻ ውሳኔው ፍጹም ኾኖ አንዱ እንደሚበቃ በአንደበቱ ባሰናኘው ቃል ግጥም ገልጿል፡፡ "የተናገረው አንዱ የሚበቃ" የሚለው አባባል በሌላ መንገድ ሲተረጎምም ግለሰቡ ሐሰት፣ ከእውነት የራቀ ነገር የማይናገር፣ ዕብለት የማይታይበት መኾኑን እንገነዘባለን፡፡ በዚህ መሠረት ቃል ግጥሙ ለተከታዩ ትውልድ የአነጋገር ሥርዓትን በማስተማር ረገድ ተግባራዊ የሕይወት መመሪያ በመኾን ማገልገል ይችላል ማለት ነው፡፡

*ቃል ግጥም 8፦ ቀብር ቀብር አሉ ቀብር ምን አለበት*
*መልካም ሥራ ሠርተው ኼደው ቢተኙበት፡፡*
*(ቃለ መጠይቅ፣ ሙሐመድ እንድሪ፣ 23/05/2012)*

አንድ ሰው ክፉ ሥራን የሚሠራ ከኾነ ቅጣትን የሚቀበል፣ ሌላው ሰው ደግሞ ምርጫው መልካም ሥራ ከኾነ ደግ ወይም ጥሩ ነገርን ከፈጣሪው የሚያገኝ መኾኑን ከማኅበረሰቡ የቃል ግጥሞች አስተምህሮ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ መሠረት ከላይ በቀረበው ቃል ግጥም ማለፊያ ወይም መልካም የኾነ ሥራን የሠራ ሰው ነፍሱ ከሥጋው ተለይታ አስከሬኑ ወደመቃብር ከወረደ በኋላ ሲፀነስ ጀምሮ በሥጋው ያደረችው ሕይወቱ ጻድቃን እስከምጽኣት ድረስ ይኖሩበታል ተብሎ በሚታሰበው የገነት ቦታ እንደምትቀይ ተገልጿል፡፡ በዚህ የተነሣ አስከሬኑ በመቃብር ውስጥ ዐፈርና ድንጋይ የሚጫነው ቢኾንም የማይጎዳና የማይቸገር መኾኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ ተቃራኒ በኾነ መልኩ ቃል ግጥሙ ሲፈከር ደግሞ ክፉ ሥራን የሠራ ሰው ከሞተ በኋላ ክፉዎች የሥራቸውን ዋጋ ያገኙበታል ተብሎ ወደሚታሰበው ወደገሃነም ነፍሱ እንደምትገባ ማጤን አስፈላጊ ይኾናል፡፡ በመኾኑም ቃል ግጥሞች ልጆች መልካም የኾኑ ምግባሮችን መከተል፣ ከክፉ ነገሮች ኹሉ መራቅ እንደሚገባቸው የሚያስተምሩ መኾናቸውን ከላይ ከቀረበው ማብራሪያ መገንዘብ ይኖርብናል፡፡

*ቃል ግጥም 9፦ መገን ያቺ ቆንጆ የምታቀርበው ማድ*
*ሁሉም ይበላዋል አይለይበትም ባዳና ዘመድ፡፡*
*(ቃለ መጠይቅ፣ ፈንታነሽ አብዱ፣ 20/05/2012)*

“ሰው ብቻውን ይኾን ዘንድ መልካም አይደለምና ረዳት እንፍጠርለት” (መጽሐፍ ቅዱስ፣ ዘፍጥረት፣ 1980፣ 2፥18) የሚለው የፈጣሪ ቃል ለማኅበራዊ ኑሮ መሠረት መኾኑ የሚታወቅ ነው፡፡ ይህ ማለት ፈጣሪ ሰውን በኑሮው በኩል ከሌላው ሰው ጋር እንጂ ብቻውን በሕይወት እንዲኖር ያልፈጠረው መኾኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ መነሻነትም የሰው ልጅ እስካሁን ድረስ ከሌሎች ጋር መኖርና ከእነሱም ጋር በማኅበራዊ ሕይወት ተባባሪ መኾን ችሏል ማለት ነው፡፡ ከላይ በለቅሶ ወቅት በተገጠመው የሙሾ ቃል ግጥምም ውብ የኾነች አንዲት ሴት በሕይወት በነበረችበት ወቅት በማኅበራዊ ኑሮዋ ከሌሎች ጋር ተባባሪ በመኾኗ የተነሣ “ይሄ የሥጋ ዘመዴ ያልኾነ ባዕድ ነው፤ ይሄ ደግሞ በትውልድ የአባቴ ወይም የእናቴ ወገን ነው” ብላ ሳትለይ ሁሉንም በአንድነት በማየት ምግብ አዘጋጅታ ታበላ እንደነበር ተገልጿል፡፡ በመኾኑም በቃል ግጥሞች ከማኅበራዊ ዕሴቶች መካከል አንዱ የኾነውን ለጋስነት ለቀጣይ ትውልድ ማስተማር እንደሚቻል መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከላይ ከቀረበው ትንተና ጋር በይዘት ተመሳሳይነት ያለውን የሙሾ ቃል ግጥም በተጨማሪነት ቀጥለን እንመልከት፡፡

*ቃል ግጥም 10፡- አትጨክኝም ነበር ሰው ታመመ ቢሉሽ*
*ልብስ፣ ምግብ፣ ገንዘብ ተቸገረ ቢሉሽ*
*ካለሽም መንዝረሽ ካጣሽ ተበድረሽ*
*ወዲህ ወዲያ ብለሽ አለዚያም ለምነሽ፡፡*
*ክፉ እንኳን አልነበርሽ ትረጂኝ ነበረ*
*ዛሬ ብትለይኝ ሁሉም ነገር ቀረ፡፡*
*(ቃለ መጠይቅ፣አካሉ ወደደኝ፣ 21/05/2012)*

የሙሾ ቃል ግጥሙ ለጋስ የኾነች ሴት በሞተች ጊዜ በአውራጅ አማካይነት የተቀነቀነ ነው፡፡ ከግጥሙ አኳያ ሴትዮዋ በሕይወት በነበረችበት ዘመን በማንኛውም ነገር ራሮት የሚሰማት መኾኑን እንገነዘባለን፡፡ በመኾኑም የቃል ግጥሙ አውራጅ በቀጥታ ስላቀነቀነለት ችግረኛ ሰውና ለችግረኛውም እርዳታ ስላደረገችለት ሴት ለአንድ አፍታ በዓይነ ኅሊናችን እንድንመለከታት አድርጎናል፡፡ በዚህ መሠረት ችግረኛ የኾነው ሰው “ጤና ዐጣ፤ በሽተኛ ኾነ፣ ወዘተ.” የሚለውን መልእክት ሩኅሩኅ የኾነችዋ ሴት ከሰማች ልቧ ስለማይጠና እንደምትረዳው ተገልጿል፡፡ በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ ሴትዮዋ ከችግሩ በስተቀር ምንም ዓይነት ሌላ መስፈርት ስላላወጣች “ሰው” የሚለውን እሳቤ የተረዳችው የአዳም ዘር የኾነውን፣ ነፍስና ሥጋ ያለው፣ ማሰብና ማመዛዘን የሚችለውን ማንኛውንም ሰብዓዊ ፍጡር መኾኑን አንባቢያን ልብ ሊሉ ይገባል፡፡ በመኾኑም የተቸገረው ሰው ገንዘብ በማጣቱ የተነሣ “እገሌ ታረዘ፣ ተራበ፣ ተጠማ” ካሏትም በቤቷ ውስጥ ገንዘብ ካላት ለልብስና ለምግብ ከፋፍላ እንደምትደግፈው፣ ካጣች ደግሞ ከሌላ ሰው ተበድራ፣ አለበለዚያም ርዳታ አድርጉልኝ ብላ በመለመን እገዛ የምታደርግለት መኾኑ ታውቋል፡፡ በመጨረሻም ሴትዮዋ በአሁኑ ጊዜ በመሞቷ የተነሣ ያ መልካም የኾነው ተግባሯ ሁሉ ሊቀር ችሏል፡፡ ስለዚህ በገንዘብ፣ በቁሳቁስ፣ ወዘተ. ሲደገፍ የነበረው ሰው ዐጣሁ ነጣሁ፤ ባዶ እጄን ኾንኩ፤ መና ቀረሁ የሚለውን ሐሳብ በግጥሙ አውራጅ በኩል ሲናገር ተደምጧል፡፡ በአጠቃላይ የሙሾ ቃል ግጥሞቹ የማኅበራዊነትን፣

እንደዚሁም የመተባበርን ዕሴቶች ጠቀሜታ የማስተማር ፋይዳ ያላቸው መኾኑን መገንዘብ ይገባል፡፡

### 5.3. በሥራ የመትጋትን ጥቅም የማሳወቅ ፋይዳ

ጥናቱ ባካለለው ወረዳ በሚኖረው ማኅበረሰብ አንደበት የሚቀነቀኑት ቃል ግጥሞች በሥራ የመትጋትን ጥቅም ይሰብካሉ፡፡ በዚህ መሠረት የቃል ግጥሞች የሥራ ፍቅር እንዲኖር በማድረግ ለኢኮኖሚውና ለማኅበራዊው ልማት የሚያደርጉት አስተዋፅኦ እጅግ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው፡፡ ተከታዮቹ ቃል ግጥሞችም በሥራ የመትጋትን ጠቀሜታ ለትውልድ እያሳወቁ የቆዩ መኾናቸውን ቀጥለን እንመልከት፡፡

*ቃል ግጥም 11፡- ኧረ ሰዎች ሰዎች መሥራት ነው ጠንክሮ*
*ማዳበሪያ አምጥቶ መክበር ነው ዘንድሮ፡፡*
*(ቃለ መጠይቅ፣ ወንድወሰን ታረቀኝ፣ 22/05/2012)*

በቃል ግጥሙ የመጀመሪያው ስንኝ ላይ “ሰዎች” የሚለው ቃል በተደጋጋሚ ቀርቧል፡፡ ይህ የኾነበት ምክንያት የግጥሙን ርእሰ ጉዳይ ለማጠንከርና በዋናው ነጥብ ላይ ትኩረት ለመስጠት ሲባል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ “ኧረ” በሚል መነሻ አርሶ አደር ለኾኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ምክር አዘል ማስጠንቀቂያ በመስጠት ላይ አተኩሯል፡፡ ምክር አዘል ማስጠንቀቂያው አርሶ አደሮቹ አንድን ነገር በርትተውና ጠንክረው ማከናወን ያለባቸው መኾኑን ለመግለጽ ነው፡፡ ጥናቱ በተካኼደበት ወረዳ ያሉ አርሶ አደሮች ጠንክረው ማከናወን ካለባቸው ነገሮች መካከል አንደኛው በፋብሪካ የተዘጋጀውን እና የልዩ ልዩ ንጥረ ነገሮች ውሑድ የኾነውን ሰው ሠራሽ ማዳበሪያ ከመንግሥት ገዝቶ በመጠቀም ድኽነትን ማስወገድ፣ ራስን በመቻል ሕይወትን መምራትና በቂ የኾነ ሀብትን ማጠራቀም ይገባል የሚል ነው፡፡ ምክንያቱም ለሰብል ተስማሚና ጠቃሚ የኾነውን ሰው ሠራሽ ማዳበሪያ በዘርና በዐረም ወቅት ከዐፈር ጋር ቀላቅሎ የተትረፈረፈ ምርት በማግኘት ባለጸጋ ወይም ሀብታም መኾን እንደሚቻል አቀንቃኙ በአንክሮ ገልጿልና ነው፡፡

*ቃል ግጥም 12፡- የበጎቹን በጠጥ ልዛቀው በአካፋ*
*እንጀራ አይበላም ቁጭ ብዬ ሳልለፋ፡፡*
*(ቃለ መጠይቅ፣ ገንዘቤ በለጠ፣ 20/05/2012)*

የዚህ ቃል ግጥም ፈጣሪ የኾነው አርሶ አደር ኺደታዊ የኾኑ የእርሻ ተግባራትን በትጋት በማከናወን ላይ የሚገኝ መኾኑን እንገነዘባለን፡፡ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊም የኾኑት ግለሰቦች የነገሩኝ ሐሳብ ሲጨመቅ በአሁኑ ወቅት በወረዳው ውስጥ ያሉት አርሶ አደሮች በመጀመሪያ ደረጃ የቤት እንስሳት ማደሪያ ከኾነው ጋጣ ፍጋቸውን በአካፋ ያፍሳሉ፡፡ ቀጥሎም ፍግን ቀድሞ በተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ ከሌሎች ቅጠላ ቅጠሎች ጋር ከጨመሩ በኋላ ለኹለት ወራት ያኽል ከውሃ ጋር በማዋሓድ ብስባሽ (Compost) ያዘጋጃሉ፡፡ ከዚያም የዘር ሥራ ከመካኼዱ ከአንድ ወር በፊት ደጋግመው ወዳረሱት ማሳ በተደጋጋሚ ብስባሹን በጆንያ እየተሸከሙ ካደረሱ በኋላ እየበተኑ ከዐፈሩ ጋር እንዲቀላቀል ያደርጋሉ፡፡ እነዚህን ተከታታይነት ያላቸውን ተግባራት ሳይታክቱ የሚያከናውኑት ብስባሹ በውስጡ በያዛቸው ንጥረ ነገሮች

አማካይነት ሰብሎቹ ዳብረው የተትረፈረፈ ምርት ማግኘት ስለሚችሉ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት የሥራ ኺደት በመትጋት ፋንታ ዝም ብለው የሚቀመጡ አርሶ አደሮች ግን እንጀራ መብላት፣ ከዚያም ዐልፎ ሀብት ማግኘት እንደማይችሉ ገጣሚው ባቀነቀነው ቃል ግጥም አስረድቷል፡፡ በዚህ መሠረት "እንጀራ አይበላም" የሚለው ሐረግ አንድም ጠንክሮ የማይሠራው አርሶ አደር ወቅት ጠብቆ ምግብ አለመመገቡን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለመተዳደሪያ የሚኾን ሀብት አለማግኘቱን ለማመልከት ነው፡

*ቃል ግጥም 13፡- ሀገር ጥሎ መኼድ ምን ያደርግልሃል*
*ጠንክረህ ብታጭድ ላንተው ይጠቅመሃል፡፡*
(ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤትቤት *የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 19/05/2012)*

ሰዎች የትውልድ ሀገራቸውን ለቀው ወደሌላ ከሚሰደዱባቸው በርካታ ምክንያቶች መካከል አንደኛው ኢኮኖሚያዊ ችግር መኾኑን ቃል ግጥሙ ይጠቁማል፡፡ ስደት ደግሞ የተሻለ ኑሮ በመኖር ረገድ ጥቅም አለው ተብሎ ቢታመንም ከወገን በመራቅ፣ ላገሩ እንግዳ ለሰው ባዳ ወይም ባይተዋር በመኾን፣ ለአዲስ ባህል በመጋለጥ፣ ወዘተ. ረገድ ከፍተኛ የኾነ ጉዳት ይኖረዋል፡፡ በዚህ መሠረት ገጣሚው አጠገቡ ላለና ሀገሩን ለቆ ወደሌላ ቦታ ለመኼድ በአእምሮው ውስጥ ላቀደው ሰው "ስደተኛ መኾን ምንም አይሠራልህምና ቢቀርብህ ይሻልሃል" የሚለውን ምክር የሰነዘረ መኾኑን ከመጀመሪያው ስንኝ መረዳት ይገባል፡፡ በመጨረሻም ገጣሚው ከመሰደድ ይልቅ ጠንክረህ ሰብልህን የማጨድ ተግባር ብታከናውን ይበጅሃል የሚለውንም ሐሳብ ሰጥቷል፡፡ ሰብልን ከማጨድ በፊት ግን ማረስ፣ መዝራትና ማረም የሚባሉ ኺደታዊ የአርሶ አደሮች ተግባራት ስላሉ እነዚህንም ቢኾን ወቅታቸውን በመጠበቅ ጠንክሮ መሥራት ያለበት መኾኑን መገንዘብ ያስልጋል፡፡ በአጭሩ ቃል ግጥሙ ተግቶ መሥራት ለሰው ልጅ የህልውናው መሠረት በመኾኑ ሀገርን ጥሎ መሰደድ እንደማይገባ ያስገነዝባል፡፡

*ቃል ግጥም 14፡- ዐረሙን ዕረሙ በጣም ተጣጣሩ*
*ችግርን በፍጥነት እንዲታባርሩ፡፡*
*(ቃል ግጥም፣ ዘይነባ ይማም፣ 23/05/2012)*

ጥናቱ በተካኼደበት ወረዳ ያሉ አርሶ አደሮች ያሉባቸውን ችግሮች ማስወገድ የሚችሉት ተግተው ሲሠሩ እንደኾነ ቃል ግጥሙ ያመለክታል፡፡ በመኾኑም አርሶ አደሮቹ ወቅት ጠብቀው የእርሻ መሬታቸውን ከገመሱ፣ ካየሙ (በተደጋጋሚ ካረሱ) እና ዘር ከዘሩ በኋላ ከእኽሉ ጋር ዐብረው የሚበቅሉትን እና አስፈላጊ ባለመኾናቸው የተነሣ የሚታረሙትን ዕፅዋት በርትተው ነቅለው እንዲጥሉ ገጣሚው ይመክራል፡፡ ዐራሙቻው በወቅቱ ተነቅሎ ካልተጣለ ግን ሰብሉ በሚገባው መጠን ስለማያድግ አርሶ አደሮቹ አጥጋቢ የኾነ ምርት ሊያገኙ አይችሉም፡፡ ስለዚህ በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ለፍተውና ደክመው የእርሻ ተግባራቸውን ካከናወኑ የተትረፈረፈ ምርት ስለሚያገኙ ከድኽነትና ከዕጦት በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊላቀቁ እንደሚችሉ ገጣሚው ገልጿል፡፡

*ቃል ግጥም 15፦ ሁል ጊዜ ደግፉኝ እናት አባት ደክሟል*
*በእጅም በእግርም ሠርቶ ራስን መቻል፡፡*
*(ቃለ መጠይቅ፣ ፈቃዱ ጤናው፣ 22/05/2012)*

ከመጀመሪያው ስንኝ ኹለተኛውን ሐረግ በተለያየ መንገድ መፈከር የሚቻል ይመስለኛል፡፡ አንደኛው ፍካሬ "ሁል ጊዜ ደግፉኝ" የሚለው ሰው ወላጆች ብርታትና ዐቅም ዐጥተዋል፤ አርጅተዋል፤ ጉልበታቸው ዐልቋል የሚል ሲኾን፣ ኹለተኛው ደግሞ ለልጃቸው ድጋፍ ማድረግ ተስኗቸዋል፤ ታክቷቸዋል ወይም ሰልችተዋል የሚል ነው፡፡ በኹለቱም ትርጓሜ ቢኾን ማንኛውም ከአብራክ የተገኘ አካል እናትና አባቱን ዘወትር አግዙኝ ወይም ደግፉኝ ከማለት ይልቅ በአጭር ታጥቆና እግሩ እስከከሚነቃም ድረስ ኼዶ ተግቶ መሥራት እንዳለበት ቃል ግጥሙ ያስረዳል፡፡ በግጥሙ ውስጥ "ራስን" የሚለው ቃል የተጠቀሰው በቤተሰብ እርዳታ የሚኖረውን ሰው በአጽንዖት ለመግለጽ በሚያገለግል ተውላጠ ስም (የስም ምትክ) ለማመላከት ሲኾን፣ ይህ ሰው በርትቶ ወይም ጠንክሮ ከሠራ ራሱን በራሱ ማስተዳደር እንደሚችል፣ ያጋጠመውን ችግርም እንደሚቋቋም፣ የሌላውን ሰው እርዳታ ከመሻት እንደሚድን ከቃል ግጥሙ መገንዘብ ይቻላል፡፡

### 5.4. መጥፎ ጠባያትን የመግታት ፋይዳ

መጥፎ የኾኑ የሰው ልጅ ልማዶችን ለመቆጣጠርና ለመግታት የሚያስችሉ ቃል ግጥሞች በማኅበረሰቡ አንደበት ሲነገሩ ይደመጣሉ፡፡ በዚህ መሠረት ማኅበረሰቡ ምስጉን እና ድንቅ ናቸው ከሚላቸው ዕሴቶች የሚያፈነግጡትን፣ እንደዚሁም ተግባራቸው መጥፎ የኾኑትን ሰዎች አድራጎታቸውን ለመቆጣጠርና ለመግታት ሲባል በቃል ግጥሞቹ አማካይነት ግሣጼ ያደርስባቸዋል፡፡ ጥናቱ በተካኼደበት ወረዳ መጥፎ ጠባያትን በተመለከተ እየተነገሩ ያሉት የቃል ግጥሞችም በስንፍና፣ በዳተኝነት፣ በሐሜት፣ በክሕደት፣ በአመንዝራነት፣ ጠንቋይን በማመን፣ በመታበይ (በመኩራት)፣ በመዋሸት፣ በሙስና፣ ወዘተ. ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ማኅበረሰቡ እነዚህ መጥፎ ተግባራት ወደተከታዩ ትውልድ እንዳይሸጋገሩ የሚገታባቸውን ቃል ግጥሞች ቀጥለን እንመልከት፡፡

*ቃል ግጥም 16፦ ቃጤ እኽል ዘርተሽ ቃጤ ካወጣሽ*
*እግዚአብሄር ይማርሽ ዐፈር በካሽ፡፡*
*(ቃለ መጠይቅ፣ ገንዘቤ በለጠ፣ 20/05/2012)*

ዐፈር ገፊ የኾነችዋ ሴት በስንፍናዋ የተነሣ ከእርሻ ሥራ ያገኘችው ምርት ከዘራቻው ዘር ጋር መሣ በመሣ (እኩል በእኩል) ኾኗል፡፡ ይህንን የታዘበው ገጣሚ ውጤት አልባ ለኾነው ሥራዋ ገላዋን ዐፈር ስለነካው "የኹሉ የበላይ የኾነው አምላክ ይቅር ይበልሽ" ብሏታል፡፡ ሴትዮዋ የእርሻ መሬቷን በተደጋጋሚ አሳርሳ ማለስለስ አልቻለችም፡፡ በዚሁ መሬት ላይም ከቁና አነስ ባለች የእኽል መስፈሪያ (ቁልቢጥ) ዘር ለክታ ብትዘራም በተገቢው ወቅት ዐረም ማረም ባለመቻሏ ዐላባው (ከማሳው ላይ ያገኘችው ምርት) ከዘራችው ዘር ጋር እኩል ኾኖ ተገኝቷል፡፡ ለውጥ ባላመጣችበት የእርሻ ተግባር አካሏ በጭቃ በመበከሉ "የሰማይና የምድሩ ጌታ በማዘን ምሕረት ያድርግልሽ" በማለት ገጣሚው በምፀት መልካሙን ተመኝቶላታል፡፡

ቃጤ እኽል ዘርታ ቃጤ እንዳወጣችው ሴት ላሉ ሰነፍ አርሶ አደሮች "ምን ያመጣል ሠኔ፤ ምን ይሠራል ቦዘኔ" የሚባለው አባባል ትልቅ ምክር የሚሰጣቸው ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም አባባሉ የሠኔ ወር ዝናብ መዝነብ የሚጀምርበት ወቅት ነው፡፡ ስለዚህ ታታሪው አርሶ አደር የእርሻ መሬቱን በወቅቱ አለስልሶ የዘር መዝራት ተግባሩን የሚያከናውንበትና ለወደፊትም አጥጋቢ የኾነ ምርት ለማግኘት መሠረት የሚጥልበት ወር ሲኾን፣ ቦዘኔው ገበሬ ግን ወቅቱን በመጠበቅ ጠንክሮ ካልሠራ ለረኃብ የሚጋለጥ መኾኑን ይጠቁማል፡፡ ከላይ የቀረበው ቃል ግጥምም ኾነ አባባሉ የስንፍናን ጠባይ በመኮነን ሥራ ፈትነት ወደተከታዩ ትውልድ እንዳይሸጋገር የማድረግ ፋይዳ ያለው መኾኑን መገንዘብ ይገባል፡፡

*ቃል ግጥም 17፦ ወገቡ ከረረ*
*ወደ ኋላ ቀረ*
*ማጭዱን ንጠቁት*
*ሚስቱ ትጨድለት፡፡*
*(ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 02/06/2012)*

በዚህ ቃል ግጥም መሠረት የዐጨዳው ተግባር ሲከናወን የነበረው በኅብረት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም "ወደ ኋላ ቀረ" የሚለው ስንኝ በቃል ግጥሙ ትችት የቀረበበት ሰው ዐብረውት ከነበሩት ዐጫጆች ጋር ሲነጻጸር ከኋላ መቅረቱን የሚጠቁም ኾኖ በመገኘቱ የተነሣ ነው፡፡ በግጥሙ የተጠቀሰው ገጸ ሰብ ግን አጎንብሶም ኾነ ተቀምጦ ሲያጭድ ከትከሻው በታች ያለው የአካል ክፍሉ ወይም ወገቡ ስለገረረ ዳተኛ ኾኗል፡፡ በዚህም የማጨድ ተግባሩን በፍጥነት ባለማከናወኑ የተነሣ ከሌሎች ጓደኞቹ ወደኋላ ሊዘገይ ችሏል፡፡ ይህንን የታዘበው ገጣሚ ደግሞ ወደኋላ የቀረው ሰው ሲያጭድበት የነበረውን ማጭድ ቀምታችሁ ለትዳር ጓደኛው ስጧትና እሷው ዐጨዳውን ታምሽክው በማለት በዳተኛው ሰው ላይ ነቀፌታ አቅርቦበታል፡፡

*ቃል ግጥም 18፡ -መንደር ለመንደር ሰው ከማማት*
*በሰዓቱ ዐጭዶ ከቤት መግባት፡፡*
*(ቃለ መጠይቅ፣ ምትኩ አገኘሁ፣ 21/05/2012)*

በዐጨዳ ተግባር ላይ የተሰማራ ሰው መንደር ለመንደር እየዞረ አንድን ሰው በሌለበት መንቀፍ፣ ስሙን ማጥፋት፣ ወይም በጥፋቱም ኾነ ያለ ጥፋቱ በክፉ ማንሣት ተገቢ አለመኾኑን በቃል ግጥሙ ተገልጿል፡፡ ከዚህ ይልቅ የማጨድ ተግባሩን በወቅቱ አከናውኖ ወደመኖሪያ ቤቱ መኼድ እንዳለበት ገጣሚው አስረድቷል፡፡ በዚህ መሠረት ሐሜት የተባለው መጥፎ ልማድ የተጠናወታቸውን ሰዎች እኩይ የሆነ ተግባራቸውን በመቆጣጠርና በመግታት ረገድ ቃል ግጥም ፋይዳው የጎላ ነው ማለት ይቻላል፡፡

*ቃል ግጥም 19፦ ማረስ ነው እንጂ በጥቋቁር በሬ*
*መንደር ለመንደር ከማውራት ወሬ፡፡*
*(ቃለ መጠይቅ፣ ሐዋ የሱፍ፣ 23/05/2012)*

ሥራውን ፈትቶ ወሬ የሚያወራውን ሰው "ወሬ ዘርግቷል፤ ወሬውን ይሰልቃል" እየተባለ በማኅበረሰቡ ዘንድ ነቀፋ ሲደርስበት ይስተዋላል፡፡ "የወሬ የለው ፍሬ"

የሚለውም አባባል ወሬ ካገኘ ለሥራ እምብዛም ግድ ለሌለው ሰው የተነገረ መኾኑን መረዳት ይቻላል፡፡ አባባሎቹ  በሰዎች መካከል የሚደረገውን ጭውውት ወይም አንዱ ለሌላው የሚያስተላልፈውን የሐሳብ ልውውጥ የሚያንጸባርቁ ሳይኾን ቁም ነገር የሌለውን ተራ ወሬ በስፋት በማውራት ላይ የሚገኘውን ሰው መጥፎ ልማድ ለመቆጣጠር የተነገሩ መኾናቸውን ልብ ልንል ይገባል፡፡ በቃል ግጥሙ ለተጠቀሰውና ወሬ ምሳው (ወሬ ወዳድ) ለኾነው ሰውም መንደር ለመንደር እየተዘዋወረ  ቁም ነገር የሌለውን እና ወጤት አልባ የኾነውን ተራ ወሬ ከማውራት ይልቅ በጠንካራ በሬዎች የእርሻ መሬቱን በመግመስ፣ በማየም፣ በመበሸል፣ ወዘተ. አለስልሶ አጥጋቢ የኾነ ምርት ማምረት አለበት በማለት ገጣሚው ገልጿል፡፡

*ቃል ግጥም 20፡- ወይ ዐርመህ አብላት ወይ አንተ ሙትላት*
*ሰነፍ ባል አግብታ ምነው ባታሰኛት፡፡*
*(ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 02/06/2012)*

ስንፍና ወይም ሥራ ጠልነት በሰዎች ዘንድ የሚኮነን መጥፎ ጠባይ ነው፡፡  ከላይ በቀረበው ቃል ግጥምም የስንፍና ጠባይ የተጠናውተው ሰው ጥፋተኛ ተደርጎ በመቅረቡ ተኮንኗል፡፡ ምክንያቱም ሰነፉ ባል መሥራት የሚገባውን  የወንድ  ሥራ በአግባቡ ባለመወጣቱ የተነሣ ነው፡፡ በመኾኑም ገጣሚው ኮትኳችና ዐራሚ የሌለው ሰብል የተትረፈረፈ ምርት ሊሰጥ አይችልም፡፡ ስለዚህ ከአዝመራህ ውስጥ የበቀለውን እና  አላስፈላጊ  የኾነውን ቅጠልና ሣር በወቅቱ ነቅለህ በመጣል የተትረፈረፈ ምርትን በማግኘት የትዳር ጓደኛህን እየመገብክና የሚያስፈልጋትን ነገር እያሟላህ አስተዳድራት፡፡ አለበለዚያ በሕይወት ኖረህ አልበጀሃትምና “ሰነፍ ባል አግብታ” እየተባለ ስሟ ከሚጠራ ሙተህ ብትቀበር ይሻላል በማለት የስንፍና ማደሪያ የኾነውን ሰው ገጣሚው አውግዞታል፡፡ በዚህ መሠረት ይህ ዓይነቱ ቃል ግጥም የስንፍናን መጥፎነት በመግታት ረገድ ጠቀሜታ ይኖረዋል ማለት ነው፡፡

*ቃል ግጥም 21፡-- ግርም ያደርገኛል ያመኑት ሲከዳ ያመኑት ሲሸሽ*
*ስብር እንደ አገዳ ሽምልል እንደ አብሽ፡፡*
*(ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 22/05/2012)*

ቃሉን የሚያጥፍና እምነት የማይጣልበት ከሓዲ የኾነ ሰው በማኅበረሰቡ ባህልና እምነት መሠረት ነውር የኾነ ተግባር እንደፈጸመ ተደርጎ የሚቆጠር በመኾኑ ነቀፋ ይደርስበታል፡፡ ከላይ በቀረበው ቃል ግጥምም ነውር ጌጡ  የኾነ ሰው በገጣሚው ወይም በሌላው ላይ ክሕደትን በመፈጸሙ ድርጊቱ የሚያስገርም መኾኑ ተገልጿል፡፡ ይኼውም ኹለቱ  ሰዎች  በጋራ ኾነው ያልጠበቁትን እና ያለ መጠራጠር የተማመኑበትን ጉዳይ  ከሓዲው  ውል በማፍረሱ ወይም በመክዳቱ የተነሣ ከአቋሙ ተንሸራትቷል፡፡ ከሓዲው  በዚህ  መጥፎ  በኾነው ድርጊቱም እንደደረቀ የአገዳ እኽል እንክትክት ብሎ መሰባበሩን፣ እንደዚሁም  በውቂያ  ጊዜ የአብሽ ገለባው በከብት እግር አማካይነት ሽምልል ብሎ መውደቁን  ቃል ግጥሙ በንጽጽር አመልክቷል፡፡

*ቃል ግጥም 22፡- ማረስ ነው እንጂ ጎራውን ዞሮ*
*ማረስ ነው እንጂ ደቡን ጎርጉሮ*
*ቀይ ሴት ቢያዩ አይኾንም ኑሮ፡፡*
*(ቃለ መጠይቅ፣ ፈንታነሽአብዱ፣ 20/05/2012)*

ከፍተኛ የኾነ ቦታን ተጉዞና ወደሌላ ቦታ ኼዶ የእርሻ ማሳውን በመግመስ፣ በማየም፣ በመበሸል አለስልሶ፣ ድብ የኾነውንም መሬቱን በመደንጎሪያ ቆፍሮ ካዘመረው ሰብል አጥጋቢ የኾነ ምርት ማግኘት የቻለው አርሶ አደር በቤቱ ውስጥ ችግርና ጉድለት የሌለበትና ማለፊያ የኾነ ኑሮ መምራት የሚችል መኾኑን ቃል ግጥሙ ያስገነዝባል፡፡ ከዚህ ውጭ ግን "በዓይኑ አይቶ በልቡ አመነዘረ" እንደሚለው የአምላክ ቃል ሥራውን ትቶ በአመንዝራነት መጥፎ ጠባዩ ከዓላማው የምታስተውን ቀይ መልክ ያላትን ሴት ሲመለከት የሚውል አርሶ አደር እኽልን ዘርቶ፣ ዐርሞ፣ ዐጭዶና ወቅቶ የሚያገኘው ምርት አይኖርም፡፡ በመኾኑም በሕይወት ዘመኑ አስፈላጊ የኾኑ ነገሮችን ስለማያገኝ አኗኗሩ ያሽቆለቁልና በችግር ምክንያት የተጎሳቆለ እንደሚኾን ከግጥሙ መረዳት ይቻላል፡፡ ስለዚህ ቃል ግጥሙ በውጫዊ ገጽታዋ መልካም የኾነችዋን ሴት በማየት የከፋ ችግር ላይ ከመውደቅ ይልቅ "በል አርፈህ ተቀመጥ" በሚል ግሣጼ ከላይ የቀረበውን መጥፎ ጠባይ ለመግታት ረድቷል ማለት ይቻላል፡፡

*ቃል ግጥም 23፡- ማረስ ነው እንጂ ዕርፉ እስኪቆመጥ*
*ዐሥር ብር ይዞ ጠንቋይ ቤት ከመሮጥ፡፡*
*(ቃለ መጠይቅ፣ ሐዋ የሱፍ፣ 23/05/2012)*

በእርሻ ሥራ የሚተዳደር አርሶ አደር ጠንክሮ ሠርቶ አጥጋቢ የኾነ ምርት በማግኘት ፈንታ ጨሌ ጣይ[5] ፣ መጽሐፍና ሞራ ገላጭ[6]፣ ሥር ማሽ፣ ቅጠል በጣሽ፣ ወዘተ. የኾነ ሰው ቤት መኼድ መጥፎ ጠባይ መኾኑን ቃል ግጥሙ ያስገነዝባል፡፡ ገጣሚው እያረሰ ያለው መሬት ምቹና ለጥ ያለ ሜዳ ሳይኾን ዳገትና ቁልቁለት፣ እንደዚሁም ጎጥ የበዛበት በመኾኑ እርሻውን ሲያርስ ዕርፉ እስከሚቆመጥ ድረስ ተግቶ በማረስ የተትረፈረፈ ምርት ማምረት እንደሚኖርበት ገጣሚው ገልጿል፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ግን የሚያስጠነቁልበትን ገንዘብ ይዞ የተለያዩ አስገራሚ ድርጊቶችን ይፈጽማል ተብሎ ወደሚነገርለት ጨሌ ጣይ፣ መጽሐፍና ሞራ ገላጭ፣ ሥር ማሽ፣ ቅጠል በጣሽ፣ ወዘተ. ቤት ቶሎ ቶሎ የሚኼድ አርሶ አደር የሚነቀፍ ተግባር እየፈጸመ ያለ መኾኑን ገጣሚው በሚገባ አስረድቷል፡፡ ከቃል ግጥሙ በተጨማሪ እንደዚህ አርሶ አደር ያሉ አስጠንቋይ ሰዎች ተግባራቸው መጥፎ መኾኑን ተገንዝበው ከአድራጎታቸው እንዲገቱ ለማድረግ "ጠንቋይ ለራሱ አያውቅ፤ የሰው ቤት ያፈርስ" በሚሉ አባባሎች ሲመከሩም ይስተዋላል፡፡

*ቃል ግጥም 24፡- ሲነግዱ አትነግድ ሲያርሱ አትረስና*
*አሟረቱብኝ በል ተኝተህ ዋልና፡፡*
*(ቃለ መጠይቅ፣ ፶ አለቃ አድማሱ ከበደ፣ 20/05/2012)*

---

[5] ጨሌ ማለት ነጭ፣ ጥቁር፣ ቀይ፣ ብጫ፣ አረንጓዴ ቀለም ያለው ባለ ቀዳዳ ጌጥ ሲሆን፣ ጨሌ ጣይ ደግሞ በእነዚህ የጌጥ ዓይነቶች የሚጠነቁል ማለት ነው፡፡

[6] ሞራ ገላጭ በጨጓራ ላይ የሚገኘውን እና ሥብ የሆነ አካል በመዘርጋት የሚጠነቁል ማለት ነው፡፡

በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ መጥፎ ጠባይ ተደርጎ የተወሰደው ሟርት ነው፡፡ ሟርት ደግሞ በሌላው ላይ መጥፎ ነገር ወይም ጉዳት እንዲደርስ ተብሎ በሰው ቤትና ዐመሬት ላይ መድኀኒትና አስማት የመቅበር ድርጊት ማለት ነው፡፡ በግጥሙ ውስጥ በመጥፎ ድርጊቱ የተኮነነው ገጸሰብ ሌሎች ነጋዴዎች እንደሚያደርጉት ሁሉ ሩቅ ሀገር ኼዶ ወይም በአቅራቢያው ካሉ መደብሮች ሸቀጦችን ገዝቶ በመሸጥ ራሱም ትርፍ ማግኘትና ለኅብረተሰቡም አገልግሎት መስጠት ሲገባው፣ እንደዚሁም የእርሻ መሬትን በማረስ፣ በማረም፣ በማጨድና በመውቃት አጥጋቢ የኾነ ምርት ማግኘት ሲኖርበት "መድኃኒት ተቀበረብኝ፣ መተት ተጣለብኝ" ማለት እንደሌለበት ቃል ግጥሙ ያስረዳል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ግለሰቡ በኑሮው ላይ መሻሻልን ለማምጣት በተለያዩ የሥራ መስኮች መታተሩን ትቶ በሰበብ አስባቡ አብዛኛውን ጊዜውን ሥራ ፈትቶ ተኝቶ በመዋል "ተሟረተብኝ" በማለት ሰዎችን ያለ ሥራቸው ወንጀለኛ ማድረጉም ቢኾን መጥፎ አስተሳሰብና ተግባር መኾኑን ከግጥሙ መገንዘብ ይቻላል፡፡

*ቃል ግጥም 25:- እነጣተ ለምለም እነ ታፋው ለምለም*
*ታሞ የተኛ ዕለት የሚቀምሰው የለም፡፡*
*(ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 02/06/2012)*

ተቀምጦ የሚውለው ሰነፉ አርሶ አደር ሥራ ባለመሥራቱ የተነሣ የእጁ ጣቶች በጣም የለሰለሱ መኾናቸው በቃል ግጥሙ ተገልጿል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይሄው የስንፍና ልማድ የተጠናወተው ሰው በዐረምና በዐጨዳ ወቅት ተቀምጦ የግብርና ሥራውን ስለማያከናውን መቀመጫውና ታፋው በዐፈርና በድንጋይ አልተፋተገም ወይም አልተፈጋፈገም፡፡ በዚህ የተነሣ ከመቀመጫው በታች ያለው የአካል ክፍሉ የለመለመ መኾኑን ከግጥሙ መረዳት ተችሏል፡፡ እንዲህ ያለው ግለሰብ ጠንክሮ አርሶ በጥሪትነት ወይም በአንጡራነት የሚያገለግል ምርት ስለሌለው ጤና አጥቶ በደዌ ዳኛ፣ ባልጋ ቁራኛ ሲያዝ እስከሚጠግብ ድረስ ሊበላ ቀርቶ ለቅምሻ እንኳን የሚኾን ምግብ ሊያገኝ እንደማይችል በግጥሙ ተገልጿል፡፡ በመኾኑም ከላይ የተጠቀሰውም ኾነ ሌሎች የስንፍና መጥፎ በሽታ የተጠናወታቸው አርሶ አደሮች ጠንክረው አርሰው የዕለት ጉርሣቸውን ማሟላትና ወደፊት ላለው ሕይወታቸው የሚኾን ጥሪትም ማስቀመጥ ባለመቻላቸው በታመሙ ወቅት የሚልሱትና የሚቀምሱት ማጣታቸው በማኅበረሰቡ ዘንድ የሚነቀፍ ተግባር መኾኑን ከቃል ግጥሙ መገንዘብ ይቻላል፡፡

*ቃል ግጥም 26፦ ጸጉርህን ከመንቀስ ልብህን ንቀሰው*
*ሚስትህን ወሰዳት ነጭ ጤፍ ያለው ሰው፡፡*
*(ቃለ መጠይቅ፣ ይመር አሰን፣ 20/05/2012)*

ቃል ግጥሙ በተነገረበት አካባቢ ባለው ማኅበረሰብ ዘንድ አንድ አባት ጎረምሳ ልጁ ጸጉሩን ካሳደገና በተለየ ኹኔታ አበጥሮ ካየው "ሚስት ዳሩኝ" የሚል ትእምርት መኾኑን ተገንዝቦ በራሱም ኾነ በዘመድ የትዳር ጓደኛ አፈላልጎ ይድረዋል፡፡ ከዚህ ውጭ ግን ትዳር መሥርቶ የራሱን ሕይወት እየመራ ያለ ሰው ያደገ ጸጉሩን ዘወትር በሚዶ አበጥሮ በመከምከም የሚዋብ ከኾነ ዓላማው ሴትን ለማማለልና ከቤቱ ያለችውን የትዳር ጓደኛውን ትቶ ወደሌላዋ ለመኼድ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ

የሴሰኛነትን ስም ያተርፋል። ይህ ዓይነቱ መጥፎ ጠባይ ደግሞ በኅብረተሰቡ ዘንድ የተጠላና የተናቀ ነው። ገጣሚው ይህንን ዓይነቱን ሰው ከዚህ አድራጎቱ ተቆጥቦ አስተዋይ፣ በሥራ የማይፈታ፣ ኃይለኛ መኾን እንዳለበት አስረድቶታል። ከዚህ ውጭ ግን የግብርና ሥራውን በመተው ጸጉሩን አሳምሮ ሌላ ሴት ሲፈልግ የሚለሰልሰውን ነጭ ጤፍ ያመረተ ሰው በሕጋዊ ጋብቻ የተጣመራትን የትዳር ጓደኛውን ነጥቆ ወደሌላ ቦታ ሊወስድበት እንደሚችል ነግሮታል። የትዳር ጓደኛውም አፍቅሮ ንዋይ የሚስተዋልባት መኾኗን ከቃል ግጥሙ መገንዘብ ይቻላል።

*ቃል ግጥም 27፦ ከቀብር ገብቼ ጎኔን ብዳብሰው*
*ከወንጀል በስተቀር ዐጣሁኝ አንድ ሰው።*
*(ቃለ መጠይቅ፣ ሙሐመድ እንድሬ፣ 23/05/2012)*

ክፉና ኀጢያተኛ የኾነው ሰው ነፍሱ ከሥጋው የተለየችው በድን ቢኾንም ከላይ ያለውን ቃል ግጥም በሰውኛ ዘይቤ ለማቀንቀን በቅቷል። ለዚህ ማስረጃውም በሞተበት ወቅት ጉድጓድ ተምሶ በቀባሪዎች ከተቀበረ በኋላ ከሌሎች ሰዎች ተለይቶ በመቃብር ውስጥ ብቻውን በቀረበት ጊዜ በመንፈስ የተናገረው በመኾኑ ነው። ንግግሩም የሚያመለክተው አስከሬኑ በመቃብር ውስጥ ከተጋደመ፣ ጉድጓዱም በዐፈርና በድንጋይ ከተሞላ በኋላ በቀኝ ወይም በግራው በኩል ያለውን የአካል ክፍሉን ቢዳብሰው በሕይወት ዘመኑ ከሠራው ኃጢያትና ከፈጸመው ወንጀል በስተቀር ሌላ ሰው ማግኘት አለመቻሉን ነው። ሟቹ ሰው "ዓለማዊ በነበርኩበት ጊዜ በሠራሁት ወንጀል የተነሣ ሰማያዊ ጸጋን ሳላገኝ ቀረሁ" በሚል የተጸጸተ ይመስላል። በዚህ መሠረት ማንኛውም ሰው እሞታለሁ ብሎ በመፍራት ለዚያኛው ዓለም መልካም የኾነ ነገር መሥራት እንጂ የፈጣሪውን ሕግ መተላለፍና የማይገባ ተግባር መፈጸም እንደማይኖርበት ቃል ግጥሙ ያስገነዝባል።

*ቃል ግጥም 28፦ ጎበዝ በጉብዝናህ ምንድን ነው ኩራቱ*
*ቆንጆ በቁንጅናሽ ምንድን ነው ኩራቱ*
*ያበለሻሽዋል እሱው ባለቤቱ።*
*(ቃለ መጠይቅ፣ አካሉ ወደደኝ፣ 21/05/2012)*

አንድ ሰው በመልክ፣ በቀለም፣... ከሱው ጋር አምሳያ ኾኖ የተፈጠረውን ወገን በኩራት መናቅ መጥፎ ድርጊት መኾኑን ከቃል ግጥሙ መገንዘብ ይቻላል። በወንድነቱ ጎበዝ የኾነ በአምሳያው፣ በሴትም ቢኾን ቆንጆ የኾነች በአምሳያዋ ላይ የኩራት ስሜት ማሳደር እንደሌለበት/ባት ቃል ግጥሙ ይገልጻል። ጉብዝና ሲባል ጉልበት ያለውን፣ ጀግና የኾነውን፣ በሥራ የሚተጋውን፣ አእምሮን በሚጠይቅ ጉዳይ ጥሩ ችሎታ ያለውን ሰው የሚያመለክት ሲኾን፣ ቁንጅና ደግሞ በውጫዊ ገጽታዋ ውብ ለኾነች ልጃገረድና ለምታምር ሴት በስያሜነት የሚያገለግል ነው። በጉብዝናም ኾነ በቁንጅና ግርማ ሞገስን የተላበሱ ሰዎች በሌሎች ላይ የሚታበዩ ከኾነ በፍጥረታት ላይ የማዘዝና የመወሰን መብት ያለው አምላክ ያለ ጊዜያቸው አበለሻሽቶ ከምድረ ገጽ ሊያጠፋቸው እንደሚችል ተገልጿል። ስለዚህ የጥናቱ አካል በኾነው ማኅበረሰብ ዘንድ በጉብዝና እና በቁንጅና በመመካት መታበይ መጥፎ ጠባይ በመኾኑ ሊገታ እንደሚገባው ቃል ግጥሙ ያስረዳል።

*ቃል ግጥም 29፦- ቀሚስ ጠፋ መሰል ሁሉም ሱሪ ለብሷል*
*ከእንግዲህ ወንድነት በምን ያስታውቃል፡፡*
*(ከባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 22/05/2012)*

ቃል ግጥሙ ገና ከመነሻው ሴቶችን በአለባበሳቸው ሲገሥጽ ይስተዋላል፡፡ ምክንያቱም አንዲት ሴት ልጅ ጥሩ ወይም መጥፎ ሥነ ምግባር እንዳላት ማኅበረሰቡ ፍረጃ ከሚያካኺድባቸው መስፈርቶች መካከል አንደኛው አለባበሷ በመኾኑ የተነሣ ነው፡፡ ቀደም ባለው ዘመን ጥናቱ ባካለለው ወረዳ ትኖር የነበረች ማንኛዋም ሴት ትለብስ የነበረው እስከ ቁርጭምጭሚት የሚደርስ ቀሚስ እንደነበር ከሕይወት ገጠመኜ በመነሣት የምመሰክረው ጉዳይ ነው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ዘመናዊነት ባመጣው ሥልጣኔ እንደከተሜዎቹ ሴቶች ኹሉ በገጠር አካባቢ ከሚኖሩት መካከል የአንዳንድ ወጣት ሴቶች የቀሚስ አለባበስ እያደር ወደባት፣ አሁን አሁን ላይ ደግሞ ከጉልበት በላይ እየኾነ መጥቷል፡፡ ይህ ዓይነቱ አለባበስ ወንድን ለመማረክ ታስቦ ነው ስለሚባል በኅብረተሰቡ ዘንድ የተናቀና የተጠላ ነው፡፡ እዚህ ላይ ከሀገራችን ባህል አንጻር የሴትነትን ተፈጥሯዊ ጾታ የሚያመለክተው ቀሚስ ከጊዜ ወደጊዜ የመለበሱ ኹኔታ እየቀነሰ መጥቶ በአሁኑ ሰዓት ሴቶች ሱሪ በመልበስ ላይ መኾናቸውን ከቃል ግጥሙ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ መሠረት ምክንያታዊ ባልኾነ መንገድ ቁሱ በአለባበስ ረገድ ባህላዊነቱን ያልጠበቀ መኾኑን እንገነዘባለን፡፡ በዚህ ኹኔታ ገጣሚው ግር ብሎታል ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ሱሪ የወንድን እና የሴትን ተፈጥሯዊ ጾታ ሊያመለክት ባለመቻሉ ነው፡፡ ከዚህ በተረፈ የቃል ግጥሙ ማዕከላዊ ሐሳብ በዋናነት ያጠነጠነው "ከእንግዲህ ወንድነት በምን ያስታውቃል" በሚለው ስንኝ ላይ ነው፡፡ ምክንያቱም ሱሪን የጀግንነት ሞያ ያለው ወንድ እንጂ ማንኛዋም ሴት የምትለብሰው ባለመኾኑ የተነሣ ነው፡፡

*ቃል ግጥም 30፦- የወንድሙን መልቀቅ ወንድሙ መውደዱ*
*ግቢው ይሰፋኛል እያለ በሆዱ፡፡*
*(ቃለ መጠይቅ፣ በለጠ አደላ፣ 22/05/2012)*

ጥናቱ በተካሔደበት ወረዳ ካሉ የጥናቱ ተሣታፊዎች የተገኘው ጭምቃ ሐሳብ እንደሚያመለክተው በሕዝብ ብዛት ምክንያት የእርሻ መሬት ከዘመን ዘመን እያነሰና እየጠበበ በመኼድ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ የተነሣ በወሰን መጋፋት ምክንያት የሥጋ ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል እንኳን ሳይቀር ጠብና ጭቅጭቅ መፈጠሩ የማይቀር ነገር ኾኗል፡፡ ይህ በመኾኑም ወንድማማቾቹ  ከአንድ እንዳልተወለዱ "ይህ ለእኔ ይገባል፤ ይህ ለእኔ መኾን አለበት፤ እስከዚህ ድረስ ያለው ደግሞ ለእኔ ይኾናል" በሚል አስተሳሰብ የወንድምን መሬት ሌላው የራስ የማድረግ ዝንባሌ ይስተዋላል፡፡

በቃል ግጥሙ እንደተመለከተውም ከእናት ወይም ከአባት ወይም ከኹለቱም የተወለደው አንደኛው ወንድ ልጅ የመኖሪያ ስፍራውን በመልቀቅ ለሕይወቱ የተሻለ ኢኮኖሚ ወደሚያገኝበት ክልል ወይም ሌላ ሀገር ሊኼድ ችሏል፡፡ ይህ ከኾነ በኋላ በቦታው ላይ የቀረው ወንድም አካባቢውን ለቆ ከኼደው ሰው መኖሪያ ቤት ግቢ ውስጥ ካለው የእርሻ ቦታ በቁመትም ኾነ በወርድ ወይም ከዙሪያው ቀንሶ በራሱ ላይ

ለመጨመር ከፍተኛ የኾነ ፍላጎት ያለው መኾኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንደዚህ ዓይነት የስግብግብነት መጥፎ ጠባይ የተላበሰው ሰው በማንኛውም ነገር መከታ የሚኾነው ወንድሙ በዚያው በወጣበት እንዲቀር እንጂ በሰላምና በጤና ወደትውልድ ሀገሩ እንዲመለስ ለፈጣሪው ጸሎት ሲያቀርብ አልተስተዋለም፡፡ ቤተሰቦች ካሉትም እነሱን ለመንከባከብ አልፈለገም፡፡ "እኔን ከተመቸኝ" በሚል አጉል ፍልስፍና ተሸብቦ የወንድሙን መሬት በቁሙ ለመውረስ መጓጓቱ ጸያፍ ተግባር ስለኾነ ሊገታ እንደሚገባ ቃል ግጥሙ ይጠቁማል፡፡

*ቃል ግጥም 31፡- ኧረ ውሼታሜው ትዋሻለህ አሉ*
*ገደልኩት ያልከው ሰው ገበያ ታየ አሉ፡፡*
*(ቃለ መጠይቅ፣ ፈቃዱ ጤናው፣ 22/05/2012)*

ውሽታም ሰው "ውሸቱ በቁመቱ ልክ ነው፡፡ ውሸቱ ቆሞ ይኼዳል፡፡ ውሸት 'ጽድቁ'፡፡ በጣም ዋሾ ነው፡፡" በሚሉ አባባሎች ሲገሠጽ ይስተዋላል፡፡ በቃል ግጥሙ እንደምንመለከተው "ኧረ" በሚለውና መገረምን ለመግለጽ በሚያገለግለው ቃል መነሻነት ዕብለት (ውሸት) ወዳድ የኾነውን ሰው "ውሼታሜው" በማለት በቀጣፊነቱ፣ በመልቲነቱ፣ በቆርጦ ቀጥልነቱ፣ ወዘተ. ሊወገዝ ችሏል፡፡ በመቀጠልም "ውሸትና ሥንቅ እያደር ይቀላል" እንዲሉ በቃል ግጥሙ የሐሰተኛ ጠባይ ያለው ሰው በውሸት ሕይወቱን አጥፍቼዋለሁ ብሎ ያወራበት ግለሰብ የንግድ ልውውጥ በሚካኼድበትና ሕዝብ በበዛበት የገበያ ቦታ ላይ በአካል በመገኘቱ ዐባይነቱ ወይም ዋሾነቱ ተረጋግጧል፡፡ ከላይ ባለው ግጥም መሠረት በቀጥታ በተባለው ጉዳይ መነሻነት የማይኾነውን ኾኗል እያሉ ከመናገርና "የበሬ ወለደ" ወሬን ከማውራት ይልቅ እውነተኛና ትክክለኛ ኾኖ የተረጋገጠውን ነገር ማውራት ተገቢ መኾኑን መገንዘብ ይገባል፡፡ በአጠቃላይ ማኅበረሰቡ መዋሸትን በመጥፎነቱ ተጽይፎ ቀጣይነት እንዳይኖረው በቃላዊ ግጥሙ እየታገለ ያለ መኾኑን መረዳት ተችሏል፡፡

*ቃል ግጥም 32፡- ለሰባት ኮሚቴ ሰባት ብር ዐጥቼ*
*ያለ በቆሎ እሸት ከረሙ ልጆቼ፡፡*
(ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ቤት የተገኘ ጽሑፋዊ መረጃ፣ 22/05/2012)

ከቃል ግጥሙ መገንዘብ እንደሚቻለው በሙስና የተነሣ ሕዝብን እንዲያስተዳድር ኃላፊነት የተሰጠው ወገን በአንድ በኩል ሥልጣኑን አላግባብ በመገልገል ራሱንም ኾነ ከእሱ ጋር ቀረቤታ ያላቸውን ሰዎች የመጥቀም፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሌላውን ሰው ችግር ላይ የመጣል ተግባር መፈጸሙን እንመለከታለን፡፡ ይኼውም ከሕዝቡ መካከል የተመረጡት የቀበሌ ገበሬ ማኅበራት ኮሚቴዎች ፍትሓዊነት ባለው መልኩ የእርሻ መሬትን ለአርሶ አደሩ ባለማከፋፈላቸው የተነሣ ግፍ የተፈጸመበት ግለሰብ ከላይ ያለውን የብሶት ቃል ግጥም ለማንጎራጎር በቅቷል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ለኮሚቴዎቹ የኪስ ገንዘብ የሸጎጠው ሰው ለም የኾነ መሬት በሙስና ሲሰጠው፣ ድኻው ደግሞ ለመማለጃ የሚኾን ገንዘብ መስጠት ባለመቻሉ ሲታረስ ጥሩ ምርት ሊሰጥ የሚችል መሬት ሊያገኝ አልቻለም፡፡ በዚህ ምክንያት ያጥንቱ ፍላጭ የሥጋው ቁራጭ የኾኑት ልጆቹ ያለ በቆሎ እሸት መክረማቸውን ተበዳዩ ግለሰብ በቃል ግጥሙ ገልጿል፡፡ በአጠቃላይ በቀበሌ ገበሬ ማኅበራት አመራር ላይ ኾነው መጥፎ

በኾነው የሙስና ተግባር የተዘፈቁ ሰዎች አድራጎታቸውን ለመቆጣጠርና ለመግታት ሲባል በቃል ግጥም አማካይነት ሲወገዙ ይስተዋላል።

*ቃል ግጥም 33፡- ማረስ ነው እንጂ እጅ እስኪቆስል*
*ስርቆት ምንድን ነው ውሻ ይመስል።*
*(ቃለ መጠይቅ፣ ፈንታነሽ አብዱ 20/05/2012)*

*ቃል* ግጥሙን ያቀነቀነው አርሶ አደር በመጀመሪያው ስንኝ ላይ የ*ሥራ መሥሪያ* የኾነው እጁ እስኪላጥ፣ እስኪደማና ጉዳት እስኪደርስበት ድረስ ለእርሻ *ሥራ* በሚያገለግሉ *መሣሪያዎች* መሬትን አርሶ በማለስለስ አጥጋቢ የኾነ ምርትን ማግኘት እንደሚገባ ጀግንነትን ወይም ወኔን በሚቀሰቅስ ኹኔታ ገልጿል፡፡ በኹለተኛው ስንኝ ላይ ግን በምን ምክንያት ነው ብሎ በመጠየቅ ቤትን ቆፍሮ፣ ሰርስሮ ወይም ነድሎ የራሱ ያልኾነውን ንብረት ደብቆ የሚወስደውን፣ እንደዚሁም ሳይታይ የሰውን ኪስ በርብሮ ገንዘብ የሚሰርቀውን ሌባ ድርጊቱ መጥፎ በመኾኑ በጽኑ አውግዞታል፡፡ በግብሩ ከውሻም *ጋ*ር በማነጻጸር በልክስክስነቱ በሰዎች ዘንድ እንዲነቀፍ አድርጎታል፡፡

## 6. *ማጠቃለያና የይሁንታ ሐሳቦች*

ይህ ጥናት "የቃል ግጥሞች ማኅበራዊ ፋይዳ - በደቡብ ወሎ ቦረና ወረዳ አርሶ አደሮች ማንጸሪያነት" በሚል ርእስ የተካኼደ ሲኾን፣ ዓቢይ ዓላማውም ከመስክ የተሰበሰቡትን ቃል ግጥሞች በይዘት መመደብና ፋይዳቸውንም መመርመር ነው፡፡ ጥናቱ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን እና ገላጭ የምርምር ዓይነትን የተከተለ ሲኾን፣ የዓላማ ተኮርን እና የጠቋሚ የንሞና ዘዴዎችን በአገልግሎት ላይ እንዲውሉ አድርጓል፡፡ በእነዚህ የንሞና ዘዴዎች አማካይነት ጥሬ መረጃዎቹ በቃለ መጠይቅና በሰነድ ፍተሻ ከተሰበሰቡ በኋላ በተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ተተንትነዋል፡፡ ከትንተናው የተገኙት ውጤቶችም እንደሚከተለው ቀርበዋል::

ጥናቱ ባካለለው ወረዳ በሚገኙ አርሶ አደሮች አንደበት የሚቀነቀኑት ቃል ግጥሞች የማኅበረሰቡን መልካም ዕሴቶች ለተከታዩ ትውልድ የማስተማር ፋይዳ እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህም ሞራልን ወይም ግብረ ገብነትን፣ እንደዚሁም ጥሩ ወይም መልካም *ሥራ*ን የሚያንጸባርቁ ዕሴቶችን በቃል ግጥሞቹ አማካይነት ልጆችን እና ወጣቶችን በማስተማር ገና ከለ*ጋ*ነታቸው ጊዜ ጀምሮ ባሕርያቸውን መቅረጽ እንደሚገባ መረዳት ተችሏል፡፡ ቃል ግጥሞች በ*ሥራ* የመት*ጋ*ትን ጥቅም ለማኅበረሰቡ የማሳወቅ ፋይዳ እንዳላቸውም ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በዚህም የቃል ግጥሞቹ በማኅበረሰቡ ዘንድ የ*ሥራ* ፍቅር እንዲኖር በማድረግ ለኢኮኖሚውና ለማኅበራዊው ልማት የሚያደርጉት አስተዋፅኦ እጅግ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ኾኖ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም ቃል ግጥሞቹ መጥፎ ተግባራትን የመግታት ፋይዳ እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህ መሠረት ቃል ግጥሞቹ በስንፍና፣ በዳተኝነት፣ በሐሜት፣ በክሕደት፣ በአመንዝራነት፣ ጠንቋይን በማመን፣ በመታበይ (በመኩራት)፣ በመዋሸት፣ በሙስና፣ ወዘተ. በሚሉ መጥፎ ተግባራት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ማኅበረሰቡ እነዚህ መጥፎ ተግባራት ወደተከታዩ ትውልድ እንዳይሸ*ጋ*ገሩ

የሚገታባቸውን ቃል ግጥሞች የሚያቀነቅን መኾኑን ከመረጃው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በመጨረሻም ጥናቱ የተካኼደበትን ማኅበረሰብ ታሪክ፣ ማኅበራዊ ሕይወት፣ ማንነት፣ ባህል፣ ወዘተ. ማጥናት የሚፈልጉ የሥነ ማኅበረሰብ፣ የሥነ ልቡና፣ የሥነ ሰብ ተመራማሪዎች የተለያዩ ማኅበራዊ ፋይዳ ያላቸውን የቃል ግጥሞችን ሰብስበው በመረጃ ምንጭነት ቢጠቀሙባቸው የሚል የይሁንታ ሐሳብ በአጥኚው ቀርቧል፡፡ ምክንያቱም ቃል ግጥሞች ያለፈውን ነገር በማጥናት፣ የአሁኑን ለማወቅ፣ የወደፊቱንም ለማቃናት ያገለግላሉና ነው፡፡

## ማጣቀሻ ጽሑፎች


የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡1980፡፡ *መጽሐፍ ቅዱስ፣ ዘፍጥረት፡፡* አዲስ አበባ፡፡

ፈቃደ አዘዘ:: 1991:: *የሥነ ቃል መምሪያ::* አዲስ አበባ፣ ኢትዮ ጥቁር አባይ አታሚዎች::

Alembi. 2002. The Construction of the Abanyole perceptions on Death through Oral Funeral Poetry. Helsinki University, Finland.

Bascom, William. 1954. Four Functions of Folklore. *The Journal of American Folklore,* Vol.67,No.266. pp. 333-349, Apr, 2007, from http://www.jstor.org/about/terms.html.

Bauman, Richard. 1971. Differential Identity and the Social Base of Folklorre. *The Journal of American Folklore*, Vol. 84, No. 331, 31-41.

Berhanu Gebeyehu. 1998. Islamic Oral Poetry in Wollo; a Preliminary Descriptive Analysis. Addis Ababa University, A Thesis Submitted in Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Master of Arts in Literature.

Douglas, Paul. 2000. Folklore from the Grassroots. *The Journal of American Folklore,* Vol. 113, No. 447, pp. 83-86 American Folklore Society Stable.

Dundes, A. 2007. *The Meaning of Folklore:* The Analytical Essays of Alan Dundes Book Editor(s): Simon J. Bronner. Logan, Utah State University Press.

Finnegan, Ruth. 1970. *Oral Literature in Africa*. Nairobi; Kenya; Oxford University press.

**--------.** 1974. How Oral is Oral Literature? *Bulletin of the School of Oriental and African Studies*, University of London, Vol. 37, and No.1, In Memory of W.H. Whitely, PP. 52-64.

**--------.** 1977. *Oral Poetry: Its Nature, Significance and social Context. London*: Cambridge University Press.

**--------.** 2012. Oral Literature in Africa. (World Oral Literature Series: Volume 1). Cambridge: Open Book Publishers.

Green, A. Thomas, ed. 1997. Folklore፡ an Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art. Santa Barbara, California Denver, Colorado Oxford, England.

Kabira, W.and Mutahi, K. 1988. Gikuyu Oral Literature. Nairobi.

Miruka, O. 1994. Encounter with Oral Literature. Nairobi.Poetry. London, Longman.

Morris, Tracie and Jean "Binta" Breeze. 2004. *Oral Poetry and Performance in Black Culture*. University of Ca'Foscari Venezia.

Okpewho, Isidore. (ed.). 1985. *The Heritage of African Poetry*. London, Longman.

**----------.** 1992. *African Oral Literature: Background, Character, and Continuity*. Bloomington and Indianapolis; Indiana University Press.

Olajubu, O. 1978. The Yoruba Verbal Artist and His Work. *Journal of American Folklore*, Vol 91, N. 360, pp 675-690.

Peek, P.M., and Yankah, K. (Eds.). 2004. *African Folklore: An Encyclopedia (1st ed.)*. Routledge. https://doi.org/10.4324/9780203493144

**በደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን በቦረና ወረዳ የሚኖሩ የመረጃ ሰጪዎች አጭር ግለ ታሪክ**

| ተ.ቁ | የመረጃ ሰጪው ስም | ጾታ | ዕድሜ | መረጃው የተሰበሰበበት ቀበሌ | መረጃው የተሰበሰበበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ይመር አሰን | ወ | 30 | ሰኞ ገበያ ቀበሌ | 20/05/2012 |
| 2 | ፺ አለቃ አድማሱ ከበደ | ወ | 74 | አይቻል ቀበሌ | 20/05/2012 |
| 3 | አቶ ሙሐመድ ይማም | ወ | 28 | አይቻል ቀበሌ | 20/05/2012 |
| 4 | አቶ ምትኩ አገኘሁ | ወ | 76 | ቀያፈር ቀበሌ | 21/04/2013 |
| 5 | አቶ በለጠ አደላ | ወ | 25 | ዋላ ቀበሌ | 22/05/2012 |
| 6 | ወ/ሮ ሰሚራ ጌቶ | ሴ | 29 | ቀያፈር ቀበሌ | 21/05/2012 |
| 7 | አቶ ሙሐመድ እንድሬ | ወ | 35 | ከቶ ቀበሌ | 23/05/2012 |
| 8 | ወ/ሮ ፈንታነሽ አብዱ | ሴ | 35 | ሰኞ ገበያ | 20/05/2012 |
| 10 | አቶ አካሉ ወደደኝ | ወ | 27 | ቀያፈር ቀበሌ | 21/05/2012 |
| 11 | አቶ ወንደወሰን ታረቀኝ | ወ | 22 | ዋላ ቀበሌ | 22/05/2012) |
| 12 | ወ/ሮ ገንዘቤ በለጠ | ሴ | 26 | አይቻል ቀበሌ | 20/05/2012 |
| 13 | ወ/ሮ ዘይነባ ይማም | ሴ | 32 | ከቶ ቀበሌ | 23/05/2012 |
| 14 | አቶ ፈቃዱ ጤናው | ወ | 24 | ዋላ ቀበሌ | 22/05/2012 |
| 15 | ወ/ሮ ሐዋ የሱፍ | ሴ | 39 | ከቶ ቀበሌ | 23/05/2012 |